# ምዕራፍ ሰባት

ስመልፈንገስና እኔ ተለያዬን፣ የእንግሊዝ ጋዜጦች፣ ሃላፊነት የጎደለው ትንበያቸው፣ የእንግሊዝና ህንድ ሠራዊት መከፋት፣ የተከፋት ቴዎድሮስ፣ አሳዛኝ ምርኮኞች፣ የፖለቲካ መረጃ ሥራዎች፣ የስር ሮበርት አመራርና የዲፕሎማሲ ችሎታ፣ ስለ እንቅስቃሴው ማዝግም ማብራሪያ፣ የእስያ ዝሆኖች በአቢሲኒያ፣ የማጓጓዣው መስመር

ባለፈው ምዕራፍ ከተዘገቡት ሁኔታዎች በኋላ፣ ከወድ ጓደኛዬ ከስመልፈንገስ ጋር ያለንን ግንኙነት ማቆሙ ጠቃሚ ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡ ስለዚህም የሱን ድንኳን ገዛሁና፣ ወደ ጠቅላይ እዙ አካባቢ በመሄድ የስንቅና ትጥቅ ክፍሉ ሀላፊ በመደበኝ ስፍራ ድንኳኔን ከካፒቴን ስፒዲ ድንኳን አጠገብ ተከልኩ፡፡

ከጠቅላይ አዛዡ ፅ/ቤት ካምፕ እራት በኋላ፣ ማለትም በሁለት ሳምንታት የጦሩ በአንጣሎ ቆይታ ጊዜ፣ ወደ ምግብ አዳረሹ የሚደረግልኝ ጥሪ ወይም ግብዣ እየተደራረበ መጣ፡፡

የእንግሊዝ ጋዘጤኞች* ቡድን በአቢሲኒያ በበቂ መጠን ነው የተወከለው፡፡ ከዘጋቢዎችም የሚደነቁ የተማሩ እዋቂ ሰዎች ነበሩ፡፡ የሚደነቁ ስልም በቅናት በማናናቅ መልከም አልነበረም፤ እያንዳንዳቸው፣ በውነት፣ በርግጥ በየራሳቸው የሚደነቁ ሰዎች ነበሩ፡፡ ምንም እንኳን በተፈጥሮ ባሕሪያቸው አልፎ አልፎ የሚያለያያቸው ነገር ቢኖርም፣ በጣም በውሱን ጊዜዎች ብቻ ነው ሲቃረኑ የሚታዩት፡፡ እንዲያውም በየድንኳኑ ውስጥ ካለው ከእያንዳንዱ የጦር ክፍል ይልቅ በጋዘጤኞቹ ድንኳን ውስጥ ስምምነትና ሰላም ነበረ፡፡ የምወዳቸውና የማከብራቸው ሰዎች ስለሆኑ በጦሩ ውስጥ በጣም የወዳጅነት ስሜት ያላቸውና አመለ መልካም ናቸው ብዬ ባመሰግናቸው፣ እነዚህን ደጋግ ሰዎች እንደወቀስኩ እንዳይቆጠር ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ (*የእንግሊዝ ጋዜጠኞች የተወከሉት በጓደኞቼ ደ/ር ቻርለስ እውስቲን፣ D.C.L., *Times*፤ ጆርጅ ኤ. ሄንቲ፣ Esq., *Standard*፤ ወ አወን ዋይትሳይድ፣ Esq፣ *Morning Post*፤ አሌክስ ሽፐርድ፣ Esq፣ *Daily News*, .. አዴር፣ *Daily Telegraph.*[89] )

---

[89] ከጦሩ ጋር የዘለቁት ጋዜጠኞች፣ (በምዕራፍ ሰባት ማስታወሻዎች)

ምንም እንኳን የጨለማ ትንበያና ውደቀት ቢነገርበትም፣ የዘመቻው ሠረገላ በተረጋጋና በሙሉ ልብ ሁኔታ፣ በዝግታ ግን በርግጠኝነት መንቀሳቀስ ጀመረ።

በአቢሲኒያ በተነገረላቸው በየተራራው፣ በየገደሉና በየሜዳው ሞልተዋል በተባሉት የዱር አውሬዎች ሰለባ የሆኑት በጣም ጥቂት ሰዎች ነበሩ።

አንድም ሰው ግን እስካሁን ድረስ በተመረዘ ማር ወይም ሌሎች ምግቦች በመብላት የሞተ የለም፤ አንድ ሰው እንኳን የጉድጓድ ውሀ በመጠጣት የተንገላታ ወይም የታመመ የለም።

አንድም ሀውሳ[90] አልተገኘም፤ ሾሆዎች፣ ኢጋሜዎች፣ ወይም የሀዞርቲት ተወላጆች ምንም የጠላትነት ስሜት አላሳዩም፤ እንዲያውም ተቃራኒ ነው የነበረው። ሰንቅ ከፍሉ መግዛት የፈለገውን ነገር መግዛት ይችል ነበር።

ምንም አይነት ጉማሬ የፀሀይ ብርሃን በመከለል መንገዳችን አላጨለመውም፤ የራበው አንበሳ ሆነ፣ አበሽማኔ በጨለማው በግ በሚለው አይናቸው ሰዎችን አላሰደነገጡም፤ የሚያስፈራው አባብም ብርድልብሳችን ላይ አልተጠቀለለም፤ የሚያሰጠሉ ብጫ ነጠብጣብ ያላቸው፣ ፒንክ ጭንቅላት ያላቸው ዝምቦችም አልታዩም።

ገዳይ ናቸው የሚባሉት ፀፀ ዝንቦች ከአይናችንም ሆነ ከአእምሮችን ውስጥ ድራሻቸው ጠፍቷል፤ ዛልትዛልያውም[91] ቢሆን የሚርገበገቡ ክንፎቹን ዘርግቶ በፍጥነት ሾልኮ ሄዷል። ምድሩ ለአይን ውብ ነው፤ ተራራዎችም ቢሆኑ በደግነት ነበር እኛን ቁልቁል ያዩን፤ ውሀው ከኖርቶን ፓምፖች እንደልብ ነበር የሚወርደው፤ አየሩም ቢሆን እንጣሎ ከደረሰን በኋላ ጥርት ያለ ነው የነበረው።

ሆ! የሚገርም ነው! ድፍን እንግሊዝ ተደንቋል። የውሸት ነብዮቹ ከነውሸት ትንቢታቸው የማያባራውን ጩኸታቸውን ማቆም ይኖርባቸዋል።

ከሁለት ወይም ሶስት ቀን በኋላ ወደፊት እንቅስቃሴ እንደሚጀመር አጠቃላይ ትዛዝ ተላለፈ፤ በዚህ ትዛዝ ሁሉም ወታደሮች ጓዛቸውን ወደ ሰባ አምስት ፓውንድ እንዲቀንሱ፣ መኮንኖችም ቢሆኑ ጓዛቸውን ወደ ሰባ አምስት ፓውንድ እንዲቀንሱና ይዘው የሚሄዱትን ፈረሶች ቁጥር ወደ ሁለት እንዲቀንሱ ተነገረ። በተጨማሪ ትዛዝ አሰራ ሁለት ወታደሮች በአንድ ድንኳን እንዲዳበሉ፣ ሁለት መኮንኖች አንድ ድንኳን እንዲጋሩ ተወሰነ።

---

[90] የፀሀፊው ሽሙጥ፤ ስመልፈንገስ ለእንግሊዝ ጋዜጦች የፃፈውን ደብዳቤ በማስታወስ
[91] በመፅሐፍ ቅዱስ የሚጠቀስ የተለየ አጥቂ አሞራ

"አአ! የእንግሊዝና የህንድ መኮንኖች! የቀበጡ! መንግስተ ሰማያት የተወለዱ! የባላባት ልጆች! እዚህ ተደረሰ? በዚህ ትዛዝ ምክንያት በጣም ተናደዱ፤ በቁጭት ተንገበገቡ፡፡ አዋቂው ሽማግሌው የጦር አዛዥ፣ ይህንን የማይመች ውሳኔ እንጣሎ እስኪደርሱ ድረስ በሆዱ ይዞ ነበር"

"ሰባ አምስት ፓውንድ- ሰባ አምስት፣ እስኪ አስቡት! በጣም የማይሆን ትዛዝ ነው! ይህን ለምንም የማይበቃ ሰባ አምስት ፓውንድ ይዤ ከምጓዝ እዚህ ግዴታ ራሴን እንደማወርድ አገልጣለሁ!" በህንድ ለሀያ አምስት አመታት ያገለገሉት ለሰለስ ያሉትና የተመቻቸው ሜጀሮችና ኮሎኔሎች ጥላቻቸውን አቃቂር ባለው ሁኔታ ነበር የገለፁት፡፡ ሰር ሮበርት ግን ፍንክች የሚል አልነበረም፡፡ ነገር ግን እነዚህ የእንግሊዝና ህንድ መኮንኖች በተራቸው ጉዳዩን እስከመጨረሻው ድረስ ለመውሰድ ወስነዋል፡፡ ብዙዎቹ ለጦር ፅህፈት ቤቱ ለመፃፍ የዛቱ ነበሩ፤ ነገር ግን በዚያ ጊዜ ዘመቻው ይጠናቀቃል፡፡

በኮሎኔል ፋይሪ የሚመራው ቀዳሚው ወይም እሳቹ ጦር ወደፊት ተንቀሳቅሶ መንገዱን እንዲያጠራ፣ የሚያሰናከል ነገር ካለም እንዲያሰወግድና፣ ፊት ለፊት ያለውን ሁኔታ ሪፖርት እንዲያደርግ ትዛዝ ተሠጠው፡፡ ሁለት ቀናት አለፉ፤ ከኮሎኔሉ የተላከው ሪፖረት በመልከተኛ በኩል ደረሰ፡፡ በሚደነቅ ሁኔታ ተፅፏል፤ ከበድ ያለ፣ ጠለቅ ያለ፣ ባይሆን ከሚገባው በላይ ቃላት የበዙበት ቢሆንም በአላጌ ተራራማ ቦታዎች ከአንድ ሳምንት ባነሰ ጊዜ መንገድ መሥራት እንደማይቻል ይገልፃል፡፡

"በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቅ ነገር አይደለም፡፡" በማለት ፋይሪ ፅፏል፤ "ከፊት ለፊታችን ያለው፣ ህገሩ፣ በወንዞችና በሸለቆዎች የተከፋፈለ፣ የተከታታይ ተራራማ ብቻ ነው፡፡ የተራራዎቹ ዳገቶች ቀጥ ያሉ ናቸው፤ ጦሩ ወደፊት ለመንቀሳቀስ ከማሰቡ በፊት ብዛት ያለቸው እርከኖች በተራሮቹ ጎኖች ላይ መሥራት አለባቸው፡፡"

"ይህ መጥፎ ዜና ነው፡፡" አለ ናፒየር ለስፒዲ፤ "ከዋናው መንገዳች ብዙ ሳንወጣ የሚወስደን ሌላ መንገድ ይኖር ይሆን?"

ስፒዲ፣ የመጀመሪያ ማረፊያችን ወደ ሆነው ወደ እሸንጌ ሀይቅ የሚወስድ የተሻለ መንገድ ካለ በማለት ሰላዮቹን ጠየቀ፡፡

ሰላዮቹም፣ "እህ፣ መንገዱማ ቀላል ነው፤ ጦሩን በቀላሉ ወደ ሀይቁ የሚያደርስ መንገድ አለ፡፡" ብለው መለሱ፡፡ እነዚህ ተስፋ የሚሠጡ ሰዎች ከካፒቴን ኤም. ግሬጎር ጋር ተላኩ፡፡ በርግጥም ግልፅ ያለና ቀጥ ያለ መንገድ ተገኘ፤ ከታሰበው መንገድም የሚወጣ አልነበረም፡፡ ኮሎኔሉ ፋይሪ ያገሩ ተወላጆች የሚሠጡትን መረጃ ያለምንም ጥርጣሬ ተማምኖበታል፡፡

በግልፅ እንደታየው ከሆነ ግን፣ በአቢሲኒያ እውነተኛው ነገር ተነግሮ አይታወቅም:: ሁሉም አቢሲኒያውያን በጣም አስገራሚ ውሸታሞች[92] ናቸው:: ስለ ወደፊት የሀገሩ ምድር የተነገረው በሙሉ፣ በጉዟችን እንዳየነው ውሸት ሆኖ ነው የተገኘው:: በተወላጆች መረጃ ተመርኩዞ የሚቀርበው የኮሎኔል ፋይሪ ሪፖርት በሙሉ፣ እንደ ሎንደኑ ትንቢት የማይታመን ሆኖ ነው የተገኘው:: ስለ ሀገሪቱ ፖለቲካ፣ ወይም ቴዎድሮስ ስላሉበት ቦታ የሚንሳፈፉ ጭምጭምታዎችም ቢሆኑ፣ በተከታዩ ቀን በሚፃፉት አፊሻል አጭር ሪፖርቶች ውድቅ ነው የሚሆኑት::

የትጥቅና ስንቅ ሀላፊው እየተላከ፣ አካባቢውን እየቃኘ፣ መንገዱን እያጣራና መሄጃውን እሰምሮ ባይጠብቀን፣ የሚቀጥለው ቀን ስለምንደርስበት ጣቢያ ዕውቀቱ አልነበረንም::

አንድ ቀን፣ የአቢሲኒያ የወይን እርሻ ያለበት ቦታ ተገኝቷል የሚል መረጃ ይደርሰናል፤ የሀገሩ የቀደመ የሥልጣኔ ምልክት ተገኘ ማለት ነው፤ ሴቶቹ ደግሞ፣ በጠይም ውበታቸው፣ ኪሎፓትራና ዮዲት የመሠሉ፣ የንግሥቶች ክብር ያላቸው ናቸው:: እርሻው በአይን መታየት ከሚችል ርቀት በላይ ነው:: ባጭሩ ግን፣ ጦሩ የተባለው ቦታ ሲደርስ፣ ከተባለው ሁሉ የተገላቢጦሽና ተቃራኒ ሆኖ ነው የተገኘው:: ይህ፣ ሁሉም ነገር የሚያስገርም አፈታሪክና የተወሳሰበ እንቆቅልሽ ነበር!

በዚህ አስተያየት ብቸኛ አይደለሁም:: ሁሉም ዘጋቢዎች፣ ስለዚህ የተለየ ነገር ሀሳብ ሰንዝረውበታል:: የሚገርመው ነገር እንደዚህ ባለ የሚያታልል ሁኔታና ምትሃታዊ ክስተት አንድ ሰው እንዴት አድርጎ አንድ የእውነት ቃል ደግሞ መናገር ይችላል::

"ቴዎድሮስ ሊመጣ ነው::"፤ "አይ አይመጣም::"፤ "ሥጦታ ሊልክ ነው::"፤ "ወደ ቋራ እየሸሸ ነው::"፤ "ሐይቅ አጠገብ ሊመሽግ ነው::"፤ "በሽሎን ሊሻገር ነው::"፤ "ሥጦታ እየላከና ለእርቅ እየፀለየ ነው::"፤ እናም፣ አንዱንም አያደርግም:: እንዲህ አይነቱ ፍች የሌለት ሚስጥራዊ ውስብስብ፣ እንዳንዱም ቢሆን፣ ያለ ሰውየው ብልጠት የተፈጠረ አይደለም[93]::

---

[92] በሰው ሀገር ጠላት መሆኑን ዘንግቶ ሁሉም አቢሲኒያዊ መንገድ እንዲመራው ይጠብቃል? ያም ሆኖ የአመባ አላጌው ጌታ ወልደ ስላሴ፣ እንግሊዞቹ በአጠገቡ እንዳያልፉ ሌላ መንገድ እንዲነገራቸው አድርጓል:: ስለዚህ ውሸት ሳይሆን፣ ሆን ተብሎም የሚደረግ ነገር ነበር::

[93] ከዚህ በፊት፣ አፄ ቴዎድሮስ ምፅዋን ባይቆጣጠሩም፣ የሚመላለሱ ነጋዴዎችም ሆነ ሌሎች ሰዎች፣ ንጉሡን ፍራቻ አንድ መጥፎ ቃል አያወሩም ነበር:: ከውጭ ሰዎችም ጋር መታየት አይፈልጉም ነበር:: ቴዎድሮስ ሁሉንም ነገር ይሰማሉ ወይም ያውቃሉ ይባል ነበር::

እሁን ጦሩ ወደፊት እየተንቀሳቀሰ ያለበት ሁኔታ ከደረሰን፣ እስኪ ደግሞ በጥቂቱም ቢሆን፣ ስለ ሀገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ እናም የእንግሊዝ መንግሥት ጦርነት ካወጀ ቀን ጀምሮ ቴዎድሮስ ጠንክረው እንደሆነ እንመልከት፡፡

ቴዎድሮስን መግቢያው ላይ የተውናቸው፣ ከዚህ የተረገመ ዕጣ ጋር እየታገሉ እንደነበረ ነው፡፡ ዙሪያውን የከበቧቸውን የብሪያሪን[94] እጅ ያላቸውን ጠላቶቻቸውን መልሰው እያጠቁ ነበር፡፡ ሰፊው መንግሥታቸው እንደ ኢካሩስ[95] የሰም ክንፍ፣ በነበረው ጥቃትና ክዳት እየቀለጠ ነበር፡፡ በእሳት የሚቃጠሉት መንደሮችና ጎጆዎች ብርሃኑ በእኩለ ሌሊት ሰማይ ላይ እቋርጦ ይታያል፡፡ ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶችና የህፃናቱ ጩኸት እየናሩን ሞልቶታል፤ በጦርነት የሚሞቱ የሚያቃስቱ ተዋጊዎች ወደ ሰማይ ለበቀል ይጮሃል፡፡

በተለያዩ ሁኔታዎች ወደ ሰላሳ ሺ የሚጠጉ ሰዎች ተገድለዋል ነው የሚባለው፡፡ በዚህ ጊዜ ቴዎድሮስ በክፉ አይን ነው የታዩት፡፡ በተሰፋ መቁረጥ ስሜትም በመጠጥም ትክክለኛ ነገር መወሰን አልቻሉም፡፡ የቴዎድሮስ ቁጣ የቅርብ አማካሪና ጓደኞቻቸውም ላይ አላቆመም፡፡ በእውነቱ ከሆነ ጥያቄው፣ "ፈጣሪ ሊያጠፋው የፈለገውን በትክክል የማሰብ ችሎታውን ይነሳዋል" ነው ወይ፡፡ የተከፉት ቴዎድሮስ! ማንም እንደሰውየው ልቡ የተሰበረ የለም፡፡

ምርኮኞቹ በሰንሰለት ታስረዋል፡፡ በነሱ ላይ ያለው የቴዎድሮስ ጥላቻ ደግሞ እየጨመረ ነው የሄደው፡፡ ሶስት ወይም አራቱ የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ነበር፤ ወደኋላ ግን ወደ እስራት ተቀየረላቸው፡፡ የእንግሊዝና የጀርመን[96] እስረኞቹ በሕይወት አሉ፤ ነገር ግን የተንጠለጠለው ሕይወታቸው በንጉሡ እጅ ነበር፡፡ ቴዎድሮስ በቁጥጥር ሥር አድርገው ያቆዩዋቸው፣ የራሳቸው መጨረሻ ከነሱ ደህንነት ጋራ የተያያዘ ነው የሚል እመለካከት ስለነበራቸው ነው፡፡

ምርኮኞቹ፣ በኮሎኔል መርዌዘር ያላሳለሰ ጥረት ምክንያት ገንዘብ ይላክላቸው ነበር፡፡ እስር ቤትም ቢሆን ገንዘብ ሀይል አለው፤ በዚህ ምክንያትም፣ የከፋ ሊሆን የሚችለው የእስራት ሁኔታ ገንዘብ በሚያስገኘው ምቾት የተሻለ ነበር፡፡

---

94 በአፈ ታሪክ መቶ እጅ አለው የሚባል ጃይንት (ጭራቅ)

95 ኢካሩስ፣ በአየር ለመብረር በሰም የተሠራ ክንፍ አድርጎ ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ ሲል በፀሀይ ሙቀት ምክንያት ሰሙ ቀልጦ ባህር ላይ የወደቀ ሰው፡፡

96 የጀርመን እስረኞች ቁጥር ከእንግሊዝ እስረኞች ይበልጥ ነበር፡፡

የእንግሊዞች ዋና ቢሮ፣ አልፎ አልፎ ከቆንሰል ካሜሩን፣ ከመልከተኛው ራሳም፣ ሉተናንት ፕሩዶ፣ ከሰርጀን ብላንክ፣ ከቄሶች ከስተርንና ከፍላድ፣ በተጨማሪም ከቫልድማየር ደብዳቤ ይደርሰው ነበር፡፡ ሁሉም ባንድ ድምፅ ስለመከራ፣ "እየየ" የሚል መልከት ለለሚልኩ፣ የተለመደ ወይም የማያባራ ነገር ሆኗል፡፡

ካሜሩን በደብዳቤው፣ የጭንቀት ቃላቶችን በመጠቀም፣ የነፃነት ደስታ እንደማያይ አርግጠኛ ሆኖ ነው የሚገልፀው፤ ተሰፋ ቆርጧል፤ ሀዘንተኛም ነው፡፡ ምስኪን ካሜሩን!

ራሳም በጭንቀት መንፈስ፣ ሰር ሮበርት ናፒየር ቴዎድሮሰ ላይ ለሰለሰ ያለ አቋም እንዲይዝ ከልቡ ይማፀናል፤ አለበለዚያ በብቀላ ሰሜት የሞት መከራ ሊወርድባቸው ይችላል፡፡ ምስኪን ራሳም!

ሚሰተር ሰትርን ደግሞ መከራውንና ችግሩን ያሳለፈው ዘርዘር ያለ ሀገሩን የሚገልፅ ፅሁፍ እየፃፈ ነበር፤ በጣም አትኩሮት የሚሰብ፣ "Wild Boar of Ethiopia[97]"፣ የእንግሊዘ መንግሥት ላደረገው የግድየለሽነት እንቅሰቃሴ ተግሣፅ መሰጠት የሚል ነበር፡፡ ደብዳቤዎቹ ግን በእውነቱ የሚያሳዝን አፃፃፍ ነው የሚታይባቸው፡፡ የከፋው ሰተርን!

መሰርሰ፣ ፍላድ፣ ፕሪዶ፣ ብላንከና ቫልደማየር የሚገርሙ ምከር የሚሠጡ ደብዳቤዎች ነው የፃፉት፤ የእንግሊዝን ህዝብ በታቻላቸው አቅም ሰለ ህዝቡ(ኢትዮጵያውያን) ባህልና አኗኗር ለማስተማር ይሞከራሉ፡፡

አፄ ቴዎድሮሰ የጦርነቱን አዋጅ በረጋ ሁኔታ ነው የተቀበሉት፤ ጥላቻቸውን ወይም ንቀታቸውን ለመግለፅ፣ ለጦርነቱም ሆነ፣ ሮበርት ናፒየር ለሚፅፈው ደብዳቤ ምላሽ አልሠጡም፡፡ ለተወሠነ ጊዜ፣ የሰውየው ሁኔታ ሚሰጥራዊ ነበር፡፡

ሆኖም፣ ራሳም በነበረው ገንዘብ[98] አማካኝነት፣ ሰለ ንጉሡ እንቅሰቃሴና ዕቅድ፣ መረጃዎች እየሾለኩ የእንግሊዝ ካምፕ ድረሰ ይመጡ ጀመር፡፡

የሚቀጥሉት፣ የእንግሊዝ ጦር አንግሎን ለቆ ወደ መቅደላ እሰከተንቀሳቀሰበት እስከ መጋቢት 12 ድረሰ፣ ሰለቴዎድሮሰ የደረሱ መረጃዎች አጫጭር ማጠቃለያ መግለጫዎች ናቸው፡፡


---

97 ቴዎድሮስን ለመጥቀስ ነው፡፡ ቴዎድሮስ ይህን ፅሁፍ ደርሰውበት፣ ስተርን "የአራዊቶች ንጉሥ" ብሎ ሰደበኝ ብለው ተናግረዋል፡፡ ይህ ፅሁፍ መኖሩን ሊያውቁ የቻሉት በፈረንሳዩ ባርደል አማካኝነት ነው፡፡ ስተርንን በጣም የሚጠሉበት ምክንያት በዚህ ፅሁፍ ነው፡፡

98 (በምዕራፍ ሰባት ማስታወሻዎች)



*የእስረኞቹ ጎጆዎች በመቅደላ*




**CAPTIVES' QUARTERS AT MÁGDALA.**

*የእስረኞቹ መኖሪያ በመቅደላ (ካርታ) ራሳም፤*
*በጣም ጠቆር ያለው ቦታ የራስ እንግዳ መኖሪያ፣ ከሱ ቀጥሎ ጠቆር ያለው*
*የፊታውራሪ ገብርዬ ቤት ነበር።*

ታህሳስ 9፣ 1867 - ቴዎድሮስ ደብረ ታቦር ነው ያሉት፤ ብዙ ሰዎችን እየገደሉ ነው[99]፤ ይህ የአላዋቂና የጭካኔ ሥራቸው ከሰው ጋር እያለያያቸው ነው:: የሠራዊታቸውን ቁጥር ለመጨመር ሞክረው ነበር፤ ከሳቸው ጋር ለመሰለፍ የተገኘው ከፍተኛው ቁጥር ስምንት ሺ ብቻ ነው::

ታህሳስ 15 - ከራሳም የተላከ ደብዳቤ የያዘ መልከተኛ ይደርሳል፤ ደብዳቤው የሚያትተውም፣ በሸዋው ንጉሥ፣ በምኒልክ የሚመራ ብዛት ያለው ሠራዊት በመቅደላና በንጉሡ ካምፕ መሀከል ሠፍሯል፤ በምኒልክ በኩል ግልበጣ በማድረግ እስረኞቹን የማስፈታት ዕቅድ አለ:: የትግራዩ ካሳ፣ ወዳጅነት ቢያስነገርም በዚህ ጭምብል ጀርባ ግን ከፉ ነገር ለማድረግ እንዳሰበ አንዳንድ የሚያሳስቡ መረጃዎች ደርሰዋል::

ታህሳስ 19 - ስለ ትግራዩ መስፍን የቀረበው ሪፖረት መሠረተ ቢስ ሆኖ ተገኘ:: ከመስፍኑ የተላከ መልከት ካምፕ ይደረሳል፤ በመልከቱም ጥያቄው ለምን "ፈረንጆቹና እኔ ወዳጅ አንሆንም?" የሱ ጠላት የናፒየር ጠላት ነው፤ የሱ ጥቅም የእንግሊዝ ጥቅም ነው::

ታህላስ 20 - የካሳ አምባሳደር ሰናፌ ይመጣል በተደረገለት አቀባበል ደስተኛ ነበር:: ሲመለስም የእንግሊዝ አይነተኛ ወዳጅ ሆኖ ነው::

ታህሳስ 22 - ከሚስተር ፍላድ የተላከ በጣም ጠቃሚ መልከት ሰናፌ ይደርሳል:: ቴዎድሮስ በቅፅበት ከደብረ ታቦር ተጉዘው በአንድ ምት ያልተዘጋጀውን የምኒልከን ጦር አሸንፈዋል:: መቅደላም ደርሰው ከምርኮኞቹ ጋር ወደ ደብረ ታቦር ሊመለሱ ነው::

ታህሳስ 25 - አስተርጓሚው ዶከተር ክራፕ ከአስሳ ሊመለስ፣ በታህሳስ 22 አሰድንጋጭ የሆነ ዜና ይዞ የመጣውን መልከተኛ መስቀለኛ ጥያቄ ያቀርብለታል:: ሰውየውም ነገሩ ውሸት መሆኑን ይናዘዛል፤ ይህም ደብዳቤው ላይ በተፃፈው ቀን ይረጋገጣል:: እንደ ሀሰት ዜና አቅራቢው ምኒልክ ላይ ጥቃት የተፈፀመው በጥቅምት ነው፤ ከሚስተር ፍላድ የተላከው የመጨረሻው ደብዳቤ የተፃፈበት ቀን ህዳር 7 ነው::

ጥር 6፣ 1868 - የተረጋገጠ ዜና ከመቅደላ እስረኞች በኩል ይደርላል፤ ምኒልከ ምንም የመንግሥት ግልበጣ ሳያደርግ ወደ ሀገሩ ወደ ሸዋ ተመልሷል:: በንጉሡ ካምፕ በደብረ ታቦርና በመቅደላ መሀከል ባለው መንገድ ማንም የቴዎድሮስ ጠላት የለበትም::

---

99 ቴዎድሮስ ደብረታቦር በሳት ያቃጠሉበት ምክንያት (በተጨማሪ ማስታወሻዎች ምዕራፍ)

ጥር 15 - ቴዎድሮስ አስር ሺ ጦራቸውንና ሀያ መድፎችን ይዘው ወደ መቅደላ እየተጓዙ እንደሆነ ዜና ይደርሳል፡፡ የሰሜኑ መስፍን ጎበዜ፣ በርቀት የቴዎድሮስን እንቅስቃሴ እየተከታተለ እየተጓዘ ነው፡፡

ጥር 20 - ሜጀር ግራንት፣ የአባይ (ናይል) ወንዝ አሳሽ፣ ሰጦታዎችን መያዝ ወደ ትግራዩ መስፍን ተልከውን ይጀምራል፡፡ ሜጀር ግራንት በአቢሲኒያ ጥሩ አገልግሎት ነው ያበረከተው፡፡

ጥር 21 - ከራሳም የተላከ ደብዳቤ ይደርሳል፤ "ቴዎድሮስ በዝግታ ወደ መቅደላ እየተጓዙ ነው፡፡ ዋግሹም ጎበዜ ሸሽቷል፡፡ ቴዎድሮስ ለኔ በፃፉት ደብዳቤ፣ "እንደምን አለህ? ደህና ነህ ወይ? እኔ በጣም ደህና ነኝ፡፡ ምንም እትሰጋ ለርዳታ ወዳንተ እየመጣሁ ነው፡፡ ራስህን ቀና አድርግ፤ በቅርቡ ከናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡ አንድ ትልቅ መድፍና[100] ሌሎችም ረዥም መድፎች ይዣለሁ፡፡ በጣም አሸባሪ ድምፅ አላቸው፤ ነገር ግን ለማጓጓዝ ከባድ ነው የሆኑት፡፡" ዶክተር ብላንክ በፃፈው መሠሪ መልስ፣ "እኛን ነፃ ለማውጣት ወደዚህ መምጣትዎን ስንሰማ በጣም ነው የተደሰትነው፡፡ የዚህን መጨረሻ ማንም ሰው ሊያውቅ አይችልም፡፡ ሁላችንም ቢሆን ለከፉ ቀን ተዘጋጅተናል፤ ነገር ግን ምንም ቢሆን ደማችን የሚበቀልልን መኖሩን ማወቃችን ርካታ መጥቶናል፡፡"

የካቲት 2 - ካፒቴን ቻርለስ ስፒዲ (ባሻ ፈለቀ) የእንግሊዝ ጦር አስተርጓሚ[101] ለመሆን ከኒውዚላንድ ይመጣል፡፡

የካቲት 9 - በመኮንኖቹ የቀረበው መረጃ ጭብጥ እንደሚቀጥለው ይነበባል፤ "የፖለቲካ ክፍል ሀላፊው ኮሎኔል መርዌዘር ዛሬ ደብዳቤዎች ተረክቧል፤ ደብዳቤው የተፃፈው ከራሳምና ዶክተር ብላንክ በጥር 17 ሲሆን፣ የባልና ሚስቱ ፍላድ ተጨማሪ እለበት፡፡ ጥር 9፣ የንጉሡ ካምፕ ወደ መቅደላ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ እስካሁን ድረስ ሁሉም እስረኞች ደህና ናቸው፡፡ መቅደላን በጥር 8 የለቀቀ የወታደሮች ቡድን ከንጉሡ ካምፕ ጋራ ተቀላቅሏል፤ ወደ አራት መቶ የሚሆኑ፣ አውሮፓውያን ያሉበት እስረኞች ከካምፑ ወደ መቅደላ እንዲወስድ ሀላፊነት ተሠጥቶታል፡፡ ለጉዞ እንዲመች እግር ብረታቸው ተፈቶ እጃቸው ግን ታስሯል፡፡ ሚስተር ሮዘንታል እብሮ እለ ይባላል፡፡ ንጉሡ መንገዱ እንዲሠራ ራሳቸው በእጃቸው ጭምር የታቾላቸውን

100 የትልቁ መድፍ የሴባስቶፖል የብሮንዝ ቅጂ በአዲስ አበባ በቴዎድሮስ አደባባይ ይገኛል፡፡

101 ናፒየር ራሱ ስፒዲን የመረጃ መኮንን ነው ብሎ የሚጠቅሰው፡፡ ይህ ደግሞ የሚገርም አይሆንም፤ ከእንግሊዝ ሠራዊት፣ እንደ ባሻ ፈለቀ አገሩን በደንብ የሚያውቅ ሰው አልነበረም፡፡

እያደረጉ ነው[102]፤ ነፃ የሆኑት አውሮፓውያን (መድፍ ሠሪዎቹ) እንዲረዱ ተጠይቀዋል፡፡ መጠነኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ከጀዳ ወንዝ ስር ከሽለቆው ደርሰዋል፡፡ በራሳም ስሌት ከነጓዛቸው በየካቲት መጨረሻ መቅደላ እንደሚደርሱ ነው፤ ካልሆነም ካምፑን ጥለው ከመጡ ግን ባንድ ቀን ይደርሳሉ፡፡ የደላንታ ሰዎች ገባር ናቸው፤ ሌሎች ግን እንደገና ሸፍተዋል፡፡ ወታደሮቻቸው በምግብ አጥረትና በመንገዱም ምክንያት እየተንገላቱ ነው፡፡ በመቅደላ እንደሚነገረው ከሆነ፣ የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ እንደበፊተኛው ሳይሆን በደንብ ተዘጋጅቶ ቴዎድሮስን ለማጥቃት ወደ መቅደላ እያመራ ነው፡፡ በዝርዝር የተፃፈ ደብዳቤ ከእንደኛው እስረኛ በኢንግላንድ ለሚኖር ጓደኛው ተልኮ ታትሞ ይወጣል፤ ይህ ደግሞ ባልታወቀ ሁኔታ የቴዎድሮስ ካምፕ ይደርሳል፤ ደብዳቤውም በሚስተር ባርዴል እጅ ነው ያለው፡፡ ይህ ነገር መልሶ ጉዳት ያመጣል ተብሎ ሥጋት አለ፡፡"

የካቲት 12 - የትግራዩ መስፍን እምባስደር ይመጣል፡፡ ፣ ጠየም ላለው ጠቆር ያሉት ግርማዊነታቸው ተወካይ፣ በእንግሊዝ ጦር በኩል ደመቅ ያለ ትራምፔት የተነፋበት ሞቅ ያለ እቀባበል ይደረግለታል፡፡ የወዳጅነት ልውውጥ ይደረጋል፡፡

የካቲት 25 - የትግራዩ መስፍን በሀውዜን በሚገኘው እንግሊዝ ካምፕ ይደርሳል፤ ራሱ፣ በእንደበቱ አጋር የመሆን ፍላጎት እንዳለው ያረጋግጣል፡፡

የካቲት 27 - ሌላ መግለጫ ይወጣል፤ በመግለጫውም ዋግሹም ጎበዜና ምኒልክ ሁለቱም ከአፄ ቴዎድሮስ እጠገብ ናቸው፡፡ ካምፑም ቅርበት ስለነበረው የዋግሹም ጎበዜ ካምፕ የሚነድ እሳት ከአፄ ቴዎድሮስ ካምፕ ሆኖ ይታያል፡፡ ዋግሹም ወደ ቴዎድሮስ መልክት ልኳል፤ ነገር ግን ክብር የጎደለውና ድፍረት መስሎ ስለታየ፣ ቴዎድሮስ መልክተኛውን በሞት ይቀጣሉ፡፡


መጋቢት 6 - በምፅዋ የፈረንሳይ ቆንስል መሴ መንዚንጀር፣ ጦሩን እንደ ፖለቲካ እማካሪና እንደ እስተርጓሚ በመቀላቀል፣ ዋግሹም ጎበዜ[103] የእንግሊዞች ተባባሪ እንዲሆን ለመጣር ተልዕኮ ይጀምራል፡፡

የፖለቲካውን ሁኔታ በዚህ ጥቅጥቅ ባለ መንገድ ከተከታተልን በኋላ፣ ትንሽ እስተያየት መስጠት ቢፈቀድልኝ፣ ሰር ሮበርት ናፒየር በዚህ ጉዳይ፣ ራሱን መሀል ላይ ሆኖ ያገኘው፤ ማለትም፣ በቴዎድሮስ፣ ዋግሹም ጎበዜ፣ ንጉሥ ምኒልክ እና የትግራዩ መስፍን መሀከል በሚደረገው ትዕይንት፡፡ የእስረኞች ሁኔታ እየተሻለ ስለመጣ መቅደላ እስከንመለስ ድረስ እንተዋቸው፡፡

---

102 የአፄ ቴዎድሮስ መንገድ (በምዕራፍ ሰባት ማስታወሻዎች)

103 ጎበዜ የዋግሹም ገብረመድህን ልጅ ናቸው፡፡ (በምዕራፍ ሰባት ማስታወሻዎች)



*ሴባስቶፖል ወደ መቅደላ ሲጎተት!*

የሰር ሮበርት ናፒየር እዋቂነት የተረጋገጠው፣ በወታደራዊ ትዛዝ በዚህ በማይታወቅ ህገር ወደ መሀል መገስገስ ብቻ ሳይሆን፣ በረቀቀ ሁኔታ ከኢትየጵያ ገዥዎች ጋር ባደረገው ዲፕሎማሲ ጭምር ነው::

አፄ ቴዎድሮስ በራሳቸው የአስተዳደር ሁኔታ ሙሉ አቢሲኒያን መግዛት አልቻሉም:: በነበራቸው ልጓም የለሽ ምኞታቸው በአንድ ጊዜ ሠፊ ከነበረው መንግሥታቸው ውስጥ፣ እያንዳንዱ መሰፍን፣ ራስ ወይም አለቃ እየራቃቸው ነው የሄደው::

ስለዚህ ሰር ሮበርት ናፒየር ይህንን አጋጣሚ መጠቀም ነበረበት፤ ቴዎድሮስ ያጡትን የሀገሩን ተወላጆች አጋርነት ወይም ታማኝነት ለማግኘት ትልቅ ጥረት ማድረግ ነበረበት:: ሚዛናዊ የሆነው የአስተሳሰብ ችሎታው በሚደነቅ ሁኔታ ለዚህ የተመቸ ነበር::

አለቆቹ ቀሰ በቀስ የሰር ሮበርት ናፒየር ታዛዥች ሆኑ፤ መጠነኛ የሆነ የራሳቸውን ፍላጎት የሚያሟላ ነገር ያደርጋሉ፤ ያም ቢሆን በናፒየር ፖሊሲ ተቀባይ እስከሆነ ድረስ ነው:: የመስፍኑ ካሳ ሁኔታ የተረጋገጠ ነው:: የሰሜኑ ገዥ ዋግሹም ጎበዜ[104] የቴዎድሮስ ጠላት ነው ተብሎ ተነግሯል:: ቁጥሩ ወደ አርባ ሺ የሚሆን ሠራዊት ይዞ በማንኛውም ሰአት ቴዎድሮስን ለመውጋት

---

104 (በምዕራፍ ሰባት ማስታወሻዎች)

ተዘጋጅቷል፡፡ እሁን የእንግሊዘ ጦር በዋግሹም ሀገር አካባቢ ስለደረሰ፣ ለሰውየው አስፈላጊ ትኩረት መሠጠት እለበት፤ አገልግሎቱ፣ ተባባሪነቱ መልካም ፈቃዱ መረጋገጥ አለበት፡፡

መሴ መንዚንጀር ከስጦታና የሰላም ጥሪ ሀሳብ ጋር ወደ ዋግሹም ይላካል፡፡

በላሰታና እንጣሎ የሚገኝበት በእንደርታ መሀከል፣ ከእንጣሎ ለላሳ ማይሎች ርቀት፣ ሌላ የጦር መሪ ቀጥ ያለ ተራራ ላይ ካምፕ አድርጓል፤ ስሙም ወልደየሱስ ይባላል፣ የያቆብ ልጅ፣ ከታወቀ የጦር አዛዥ ይልቅ የሽፍታ አለቃ ይመስላል፡፡ ለዚሀ መሪም ቢሆን ናፒየርን መጥቶ እንዲጎበኘው የግብዣ ጥሪና የአጋርነት ወይም የገለልተኛነት ጥሪ ያለው መልከት ይልካል፡፡ ጦረኛው ወልዴ ግን የሚያወላውል መልስ ይመልሳል፡፡ ዋግሹም ጎበዜ ከመቼው በበለጠ ጉራ የመጨመር አዝማሚያ ይታይበታል፤ እርባ ሺ ወታደሮች ይዞ ማድረግ የማይችለው ነገር የለም ብሎ እሰቧል፡፡

እንደዛም ሆኖ፣ መልሶቹ እንግሊዞችን የሚፃረሩ አልነበረም፤ ባይሆን፣ መልሱ የማያረካ ራሰን ከፍ ከፍ የሚያደርግ፤ ሰላለው ሀይልና ቴዎድሮሰ ላይ ሰላለው ዕቅድ የሚገልፅ ነው፡፡

ከአጋርነት ይልቅ ገለልተኛነቱን የመረጠ ይመሰላል፡፡

"ነገር ግን፣ በበቂ ሁኔታ ከተከፈላቸው፣ የሱ ሰዎች ለኛ ወታደሮች የሚያስፈልጉትን ነገሮች እንዲሸጡልን ፈቃድ ለመሰጠት ቃል ይገባል ወይ?" ብሎ ሰር ሮበርት ጠየቀ፡፡

"እዎ፣ ሰዎች ያሻቸውን መሸጥ ይችላሉ፣ አይከለከላቸውም፡፡ ቴዎድሮሰ የናፒየርም ሆነ የሱ ደመኛ አይደለም እንዴ?"

ሰር ሮበርት በጣም ትዕግሰተኛ ሰው ሰለሆነ በቀላሉ የሚሸበር ሰው አይደለም፡፡ የማያባሩ መልክተኞችና ከዋናው ፅሀፈት ቤት የሚፃፉ የምሰጋና ደብዳቤዎች በየጊዜው ለዋግሹም ይላኩለት ነበር፤ ሰጦታዎችን ጨምሮ መልካም ምኞት መግለጫ ያላቸው ደብዳቤዎችም ነበሩበት፡፡ ማንም መሰፍን ቢሆን፣ እንደነዚሀ አይነቶችን ታላቅ ሥጦታዎችና ወደፊትም ቢሆን የሚያጋጥመውን የተሻለ ዕድል ማሰብ የሚያጓጓ ነገር ሰለሆነ አሉታዊ የሚሆንበት ነገር አይደለም፤ ሰለዚሀ ለተደረገለት ነገር በሙሉ ብድር መመለስ እንዳለበት ይሰማዋል፡፡ የእንግሊዙ ንጉሥ ትኩረት መሥጠትና ደግነት፣ የዋግሹምን ኩራት እቀዘቀዘው፤ ሰለዚሀ፣ እሱም ቢሆን ተጠራጣሪ ተፈጥሮ ቢኖረውም ለእንግሊዞቹ ሀሳብ እጁን ሠጠ፡፡

መልሶ በፃፈው ለጋስ አፃፃፍ፣ ዕቅዱን በመግለፅ ባለው ሀይሉ በሙሉ ናፒየርን እንደሚረዳና ሁኔታዎች ሲፈቅዱለት ቴዎድሮስን እንደሚወጋ አስታወቀ፡፡

ከመቅደላ ባሻገር ባለው ሀገር፣ ከሱ ጋር ሰላም መፍጠር የሚያስፈልግ ሌላ ሰው አለ፤ ይህም የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ነበር፡፡ እሱም ቢሆን ቴዎድሮስን ለማጥቃት የተዘጋጀ ወደ አርባ ሺ የሚሆን ሠራዊት አለው፡፡ ነገር ግን እንደ ጎበዜና እንደ ትግሬዩ መስፍን በአንድ ቦታ የሰከነ ሳይሆን በየቦታው የሚዘዋወር ታላቅ ገዥ ስለነበር ከሱ ጋራ ግንኙነት ማድረግ መቻሉ አጠራጣሪ ነበር፡፡

በመቅደላ ዙሪያ ባለው አገር፣ ወደ ቴዎድሮስ ምሽግ መሄጃ በግራ በኩል፣ በየቦታው የሚታዩት ኦሮሞዎች በየንግሥቶቻቸው ሥር ይገኛሉ፡፡ የአዘቦ ኦሮሞዎች በንግሥት ወርቂት፣ የወሎ ኦሮሞዎች በሞግዚቷ በንግሥት መስታውት ሥር ናቸው፡፡ እነዚህ ሙሰሊሞች ሲሆኑ እኛ ግን ክርስቲያኖች ነበርን፡፡

ሰር ሮበርት ግን፣ ለሁሉም እምነት ተከታዮች፣ ዘሮችና ተወላጆች ዝግጁ ነበር፡፡ እሱን ከሚከተሉት ሰዎች አንዱ፣ ጄኔራሉን ለመከተል ፈቃድ የጠየቀው መሀመዳዊው መስፍን ሚር አከባር አሊ[105] ነበር፡፡ ይጠቅማል በሚል እምነት እንዲከተል ተፈቅዷል፡፡ ይህ ህንዳዊ ሙስሊም፣ ከሙሰሊም ገዥዎች ጋር መደራደር የሚችል ትክክለኛው ሰው ነበር፡፡ ጠቆር ያለው የቆዳው ቀለም፣ እምነቱ፣ መልከመልካም መሆኑና ለውድ ዕቃዎች ያለው ፍቅር የሚጠቅሙት ባህሪዎች ነበሩ፤ ለዚህ ጉዳይ ወይም ሥራ ደግሞ የተመረጠውና መንቀሳቀስ የሚችለው በኦሮሞ ምድር ስንደርስ ብቻ ነው፡፡


ሜጀር ግራንት ከወልደየሱስ ጋር ላደረገው ግንኙነት መመስገን አለበት፤ ተልዕኮው ስለተሳካም፣ ወልደየሱስ የፈረንጁን ጄኔራል ለመገናኘት ወንድሙን በመላክ ለሰላም የተደረገለትን ጥሪ ተቀበለ፡፡

ካፒቴን ሙር የተባለ፣ በአረቢያና በፔርሽያ[106] የተጓዘ የአረብኛ አስተርጓሚ፣ ደበዳቤዎችንና ስጦታዎችን በመያዝ ወደ አካባቢ ገዥዎች ይላካል፤ በእንግሊዙ ጄኔራል በኩል፣ በምንም አይነት መንገድ እነሱን ለማጥቃት ምንም ዕቅድ እንደሌለ ለገዥዎቹ ለማረጋገጥ ነበር፡፡ ጥረቱም በሙሉ የተሳካ ነበር፡፡ ገዥዎቹ፤ በአንድ ድምፅ ተስፋቸው የእንግሊዙ ጄኔራል አሸንፎ ሀገሩን እንዲይዝ ነበር፤ ከሰዎች ጋር ለመደራደር የተጠቀመበት ለቀቅ

105 አከበር አሊ ምድቡ ከመረጃው ክፍል ሀላፊ ከሜጀር ግራንት ጋር ነበር

106 የአሁኑ ኢራን

ያለው የጄኔራሉ ፖሊሲ፣ ቀደም ብለው አስበውት ከነበረው ከጄኔራሉ ዕቅድ ጋር የተለያዬ ነበር፤ በልባቸው፣ ነገሮች ሁልጊዜ እንደዚህ ቢሆኑ ምኞታቸው ነበር፡፡



*ሚር አክበር አሊ*
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ስለዚህ ሽማግሌው ሆን ብሎ የዘገየበት ምክንያት ተገልጧል፡፡ ግልፅ ከሆነው የዘመቻው ጉዞ ታከቲክ በተጨማሪ፣ በሙሉ ልብ ወደ መሀል አገር ከመዝለቁ በፊት ማከናውን የሚገባው አሳሳቢ የሆኑ የዲፕሎማሲ ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ ምናልባትም በራሱ የሚተማመን ደፋርና ችኩል ጄኔራል፣ እንደ ሸርማን[107] አይነቱ ቢሆን፣ ከናፒየር በፊት ቀደም ቀጥታ ወደ መቅደላ ይገሰግስ ነበር፡፡ ያማረ የመጨረሻ ውጤት የተገኘበት የዳተኛው ጄኔራል ጥረት በችኩሉ በጄኔራል ሸርማን ተቀባይ መሆኑ በጣም አጠራጣሪ ነው፡፡

---

107 ሜጀር ጄኔራል ዊሊያም ተኩምሳ ሸርማን፣ በአሜሪካው እርስ በርስ ጦርነት በዩኒየን በኩል የነበረ ታዋቂና ደፋር ጄኔራል ነበር፡፡ ጄኔራሉ 'scortch the earth' በሚባለው ፖሊሲው ማለትም ቤቶችን በእሳት በማንደድ የሚታወቅ ነው፡፡

የስንቅና ትጥቅ ክፍል ሀላፊው የአሳሹ ጦር ሪፖርት ሲደርስ፣ ጦሩ ካምፕ ነቅሎ ከአንጣሎ ስምንት ማይሎች ርቀት ወደሚገኘው ወደ ሙጂ ተጓዘ፡፡

ፊት ለፊታችን አሉ በተባሉት ታላቅ መሰናክሎች ሪፖርት የተነሳ ሁላችንም ስለ ሀገሩ ተፈጥሮና ወደፊት በመንገዳችን ላይ ስለሚያጋጥመን ሁኔታ ጭንቀት ነበረብን፡፡ ከአንጣሎ አምባ፣ ከላይ ሆኖ የሀገሩን አካባቢ በስፋት ማየት ይቻል ነበር፡፡

ከዚህ ከፍታ ሆነን ማየት ከምንችለው ሁሉ፣ አካባቢው፣ ቀጥ ያሉ የተራሮች ሰንሰለት ያሉበት ይመስላል፡፡ ግዙፍ የሆኑ ቀላ ያሉ የተራራ ጫፎች፣ ወደ ላይ ብሩህ ሰማያዊ ቀለም ወዳለው ሰማይ የተተኮሱ ይመስላሉ፤ ግራጫ መልክ ያላቸው ግራናይት አለቶች አንዱ ባንዱ ላይ ተደራርበው ይታያሉ፤ ኮረብታ በኮረብታ እየተከታተሉ አጅብ ብለው ወይም እንደ መጋዝ ጥርስ ተደርድረው ይታያሉ፡፡ በሸለቆው መሀል፣ ከአንጣሎ ተነስቶ ወደ ጎድጓዳው ስፍራ የሚወስደው ነጣ ያለ መንገድ ይታያል፤ መንገዱም እንደ ሰማይ ላይ እንዳለ የከዋከብት ብርሀን መስመር ተለይቶ ይታያል፡፡

ወደዚህ መሰጊ ወደተባለው ቦታ የተደረገው ጉዞ አሰቸጋሪ ነው ተብሎ የሚጠራም አልነበረም፡፡ ካለንበት ከአንጣሎ ካምፕ በደልዳላ ሜዳ ላይ የሚያቋርጥ ነበር፡፡ መሰጊ ከደልዳለው ሰፍራ ዳር ላይ ያለ ሶሰት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ሲሆን፣ መሬቱም በሁለት ንፁህ ወራጅ ውሀዎች ይታጠባል፡፡

ከዚህ ቀደም እንደገለፅኩት፣ መኮንኖቹ መያዝ የሚቻለውን የጓዝ መጠን የሚጠቅሰውን ጥብቅ ትዛዝ መጣሰ ችለዋል፡፡ አብዛኞቹ መኮንኖች እያንዳንዳቸው፣ በአንጣሎ ከነበራቸው ስድሰት ሠራተኞች ምናልባትም ሁለቱ ብቻ ነው የቀሩት፤ ከአምስት የጭነት ከብቶች ሶስቱ ከነጂዎቻቸው ጋር አብረው ተጉዘዋል፡፡ ሰለዚህ በሁለቱ ካምፖች መሀል ያለውን ርቀት የሚሸፍን ትልቅ የተከታዮችና የከብቶች መሰመር ሠራዊቱን ተከትሎ ይጓዝ ስለነበር በፍጥነት የሚደረገውን እንቅስቃሴ እንዲያዘግም አድርጎታል፡፡

ከሠራዊቱ ጋር መጓዝ ትግሰት የሚያሳጥር ሆኖ ነው የተገኘው፡፡ ረዥም ዘገባዎችን መዘገብ ሙያችን ለሆነ ሰዎች፣ አድካሚ ሥራ፣ ካምፕ እንደደረሰን መታወቅ ጀመረ፡፡ ለአሰራ ሁለት ወይም እንደ ሁኔታው ለአሰራ አምሰት ሰአታት ኮርቻ ላይ ተጣብቆ፣ ጓዛችን ለመጠበቅና ለማጀብ ጎን ለጎን መጓዝ፤ ከዛም ካምፕ ከደረሱ በኋላ፣ ዘገባ መፃፍ ቀላል ሥራ አይደለም፡፡ በመንገድ ላይ ያጋጠሙ ነገሮችን መመዝገብ፣ የእለቱን የፖለቲካ መረጃ መሰብሰብን ይጨምራል፡፡ ከዚያ ደግሞ፣ የሶሰት ሰአታት የሚሆን ቁርጫ እንቅልፍ መተኛት፣ ስኳር የሌለው ሻይ መጠጣትና የደረቀ ዳቦ ጎርሶ ከጠዋቱ አሰራ

አንድ ሰአት ሲሆን የተለመደ መንገድ ለመቀጠል ኮርቻ ላይ መውጣት የሚያስደስት ሽርሽር አይደለም፡፡ ይህ ሁሉ በቀላሉ መፍትሔ ያገኝ ነበር፡፡

አንድ ሰው ሊረዳው እንደሚችለው አምስት ሺ ወታደሮች ያሉበት ሠራዊት፣ ከሚከተሉት አስር ሺ ከሚሆኑ ከብቶች ጋር በአግር መንገድ ያውም ባንድ መሰመር መጓዝ፣ አስር ማይል ለመጓዝ ሙሉ ቀን ይወስድበታል፤ ያም ምንም አከል ሳይፈጠር ወይም ጓዝ ከጭነት ላይ ካልተንሸራተተ ነው፡፡ እንግዲህ፣ ይህ ያለማቋረጥ የሚጓዘው ጦርና የሚከተለው ጓዝ፣ ሙሉ ቀን ከወሰደ፣ ያለማቋረጥ ወደ ሁለት እስከ ሰሰት መቶ የሚሆኑ በቅሎዎችን ጭነት ለማስተካከል በየጊዜው መቆም ካለበት፣ በቅሎዎችም በየሰሰት ርምጃዎች እየዘለሉና መሬት እየተኙ ጭነቱን የሚያንሸራትቱትና የማይቀል ርግማን የሚያስከትሉ ከሆነ፣ ምን ሊደረግ ነው?

በዘመቻው የሚታየው አጠቃላይ የጥበቃ ሁኔታ ከሌሎች ዘመቻዎች ጋራ ተመሳሳይ ነው፡፡ የጠዋት መቀስቀሻው ጥሪ፣ ቀኑ ሲወጣ ተሰማ፤ ቀዳሚ ጦሩም ተንቀሳቀሰ በግማሽ ሰአት ውስጥ ከሰንቅና ትጥቅ ከፍል መኮንን ጋር በመሆን መንገድ ሲጀምር ነው፡፡ ይህ የሚንቀሳቀሰው ከፍል፣ የቃኚዎች ሀላፊ ኮሎኔል ፋይሬ ከሁለት ቀን በፊት ቀደም ብሎ ተጉዟል፤ ያም ለጣቢያ ይሆናል ብሎ የወሰነውን ቦታ ለመምረጥና ምልክት ለማድረግ ነው፡፡

የመጓጓዣው ወይም ጭነቱ፣ በመኮንኖቹ ያላሰለሰ ግፊት እየተቀነሰና እየተቆነጠረ ከየሬጂመንቱ ቀድሞ ወጥቶ ነበር፡፡ ጭነቱ በበቅሎዎች ላይ ተጭኖ፣ ሰልፉ ወይም ተጓዡ እስከሚያልፍ ድረስ በየመንገዱ ዳርቻ መሰመር ይዞ እንዲጠብቅ ተደረገ፡፡

ከጥዋቱ አሰራ ሁለት ሰአት ሲሆን፣ ሁሉም ነገር ዝግጁ ነበር፡፡ የጦር ባንድ ሙዚቃ መጫወት ጀመረ፤ አግረኛው፣ ፈረሰኛው፣ ከባድ መሳሪያ ከፍሉ፣ የባህር ሀይሉ ብርጌድ፣ ዝሆኖቹና የጓዙ መሰመር ወደፊት መንቀሳቀስ ጀመሩ፡፡

እኩለ ቀን ሲሆን፣ የተጓዡ ቀዳሚው ከፍል አዲሱ ካምፕ ቦታ ደረሰ፡፡ ከሁለት ሰአታት በኋላም ጓዙ ደረሰ፤ ሆኖም ማታውኑ ሆነ እስከነጋታው ጠዋት ድረስ የሚንቀራፈፉ የጭነት ከብቶቹ እየመጡ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ፣ እንሰሶቹ ጉልበታቸው እስኪታደስ ድረስ ለአንድ ቀንም ቢሆን ጉዞ እናቆማለን፡፡ አጭር የሆነ የአምስት ወይም የሰድሰት ማይሎች መንገድ ስንጓዝ፣ መንገዱ ቀጥ ያለ ቁልቁለት ካልሆነ በስተቀር የጓዙ የመጨረሻው ከፍል ፀሀይ ሳትገባ ካምፕ ይደረሳል፡፡

የየቀኑ ጉዞ ማለቂያ ሰአት ላይ፣ የአገሩ ተወላጆች፣ ከያዙት አህል፣ ሳር፣ ምግብና ዳቦ ጋር ወደካምፑ ይጎርፉ ነበር፡፡ የየመንደሩ አለቆችም እየመጡ

ይጎበኙ ነበር፤ እና በዚህ ጊዜም ጠቅላይ አዛዡ፣ ሁሉም መኮንኖች እንዲገኙበት የሚጠበቅበት ግብዣ ያዘጋጃል።

መንገዱ ቀጥ ያለ ዳገት ከሆነ ደግሞ ዝሆኖቹ ከከባድ ሸክሞቻቸው ጋር ይታገላሉ። ያ ሲሆን፣ ሌሎቹ የጭነት ከብቶች አልፈዋቸው ይሄዳሉ። በሚስማማ መንገድ ሲሆን ግን እነዚህ ግዙፍ እንስሶች 1800 ፓውንድ ከሚመዝነው ጭነታቸው ጋር ሁኔታውን በደንብ ተቆጣጥረው በበቂ ፍጥነት ጉዟቸውን ያሳካሉ። በዚህ ጊዜ፣ ላገሩ ተወላጆች የሚያሰፈሩ አለዚያም ለማየት የሚያስደሰቱ ሆነው ነው የተገኙት። ያገሬው ሰዎች ከብብ አያሉ፣ ዝሆኖቹ በሰልፍ ቁልቁለትና ዳገቱን ሲወጡ ማየት የሚታከታቸው አይመስልም። 1500 ጫማ የሚሆን ዳገት መውጣት ለዝሆኖቹ ከባድ መሆኑ ያስታውቃል፤ የሚያሰሙት ከባድ ትንፋሽና የሚያናፋት ድምፅ የጭንቀታቸው መግለጫ ነበር። ለዘመቻው ወሳኝ ነበሩ። በየቀኑ አርባ አምስት ፓውንድ የሚሆን ዳቦ፣ አርባ ፓውንድ የሚሆን ጭድ ወይም ያገሩን ገለባ ይመገቡ ነበር። አንዳንዶች ከታወቁት የባርነም "ሃኒባል" ከሚባሉት የሚገዘፉ ሲሆኑ፣ አብዛኞቹ ግን በእንፃሩ ወጣት ስለነበሩ ድካሙን በዕደሜ ከገፉት የበለጠ ይቋቋሙት ነበር።

የሬጂመንቱ ወጥ ቤቶች ምግብ እያዘጋጁ እያለ፣ ወታደሮች በመጀመሪያ ካምፕ እንደደረሱ ከተፀዳዱ በኋላ ራሳቸውን በተለያዩ ስራዎች ጠመዱ። ጂምናስቲክና ሌሎች የሰውነት እንቅስቃሴ ይወዱ ስለነበር፣ በካምፑ ውስጥ የሚያዝናና የሚያዝናና ትዕይንት ይታይ ነበር።

ፀሀይ ስትጠልቅ፣ ከጦሩ ባንድ የብሮንዝ የሙዚቃ መሳሪያዎች ዜማ ይሰማል። ለመጀመሪያ ጊዜም፣ ዙሪያውን የከበቡት ተራሮች ይህንን የወታደራዊ ዜማ ያስተጋባሉ። እያንዳንዱ ያገሩ ተወላጅ ደግሞ የያዘውን ጦር ተመርኩዞ፣ በፀጥታ ተሸብቦ ያለምንም መግደርደር ነብሱን የሚያረጋጉ የሚመስሉ እነዚህን ተሰማምተው የሚወርዱ ዜማዎችን በደስታ ያዳምጣል። ጨለማው ሲገባ ሁላችንም እንለያያለን። ሙዚቃው በሩቅ ሲሰማ በማይገለፅ ሁኔታ ጣፋጭ ሆኖ፣ ነፍሳችን ውስጥ የትዝታ ስሜት ይረጫል፤ በዚህም ምክንያት አእምሯችን በአቢሲኒያ ተራሮች ወጣ ገባ ኮረብታዎች አልፎ ሰማያዊውን ባህር ተሻግሮ፣ በርቀት ወዳለው ቤታችን በህሳባችን እንድንጓዝ አደረገን።

መጋቢት 14፣ አንጣሎን ትተን ሄድን። መሸከ ከመሰገ ሰምንት ማይሎች ርቀት ነው ያለው። ከዚህ ከኋለኛው ካምፕ፣ መንገዱ እየተጠማዘዘ ወደላይ ከሸለቆ ጎን ለጎን ይሄዳል። ሸለቆው በጎንና ጎኑ በጣም አረንጓዴ በሆኑ ተክሎች በተሸፈኑ የኮረብታ ሰንሰለቶች ታጅቧል። በመንገዳችን ላይም ሁሉም አይነት የተፈጥሮ ዕይታ አለ። ሾጠጥ ባሉት ኮረብታዎች ላይ የከምር እሳት ይነዳል፤

ያም በጠንካራ አምባው ላይ በበረት እንደተያዘ ነብር የተቀመጠውን የአለቤ ገዥ ስለኛ መምጣት ለማስጠንቀቅ ነበር:: ከተራራዎቹ ጫፍ ላይ የጭስ ምሰሶዎች፣ መልከ ባለው ሁኔታ ወደ ላይ ከፍ ብለው ይታያሉ፤ ይህም የስማያት አማልክትን በቀል እንዲያደርጉ ለመማፀን የሚጨስ የገፀበረከት ጭስ ነው የሚመስለው:: ከየምሽጎቹ ጀርባ፣ ጠቆር ያሉ ተጠራጣሪ ሰዎች እኛን ቁልቁል ይመለከታሉ፤ ለመዝረፍና ለመግደል የጓጉ ይመስላሉ፤ ነገር ግን እንደ ብልጥ ተኩላ ያጋጠማቸውን ጥሩ ዕድል በመጠቀም ከምሽጋቸው ወርደው ከመዝረፍና ከመግደል ተቆጥበው ኢጋጣሚውን አሳለፉት::


እነስ ባሉት ኮረብታዎች በየጎጆዎች የሚኖሩት ሰዎች ግን፣ በኛ ግምት ስብስብ ብለው፣ በየዳገቱ ያልተለመደ አለባበስ ለብሰው በመገረም ቆመው ሰናይ፣ አየጎረፉ በሚሄዱት ፊታቸው ነጣ ያለ እንግዶች ምንም የጥቃት ስሜት የተሰማቸው አይመስሉም::

ካምፕ ለመድረስ ሁለት ማይሎች ርቀት ሲቀረን፣ ጠመዝማዛና ምገደኛ የሆነ ወራጅ ውሃ በየደቂቃዎች ማቋረጥ ነበረብን:: በቦታው የነበረው እነስ ያለ ሸለቆ ደግሞ እየሰፋ በመሄድ አርንጓዴ የበቆሎ ተክሎች መታየት ጀመሩ፤ በመሀሉም፣ አልፎ አልፎ ደኖችና፣ ዝቅ ያሉ ቦታዎች ላይ፣ ሜዳዎች፣ ችፍግ ባሉ ሳሮችና የተለያየ ቀለም ባላቸው በፈኩ አበቦች ተሸፍነዋል:: ተራራው በሁለቱም ጎን 1500 ጫማዎች በላያችን ላይ ከፍ ብሎ ይታያል:: ወጣ ገባ ያለው የተራራዎቹ ጎን፣ ብዛት ባላቸው ጥድ የመሰሉ ዛፎች ተሸፍኗል፤ በለውጡም የቁልቋልና ሌሎችም ተከሎች አሉባቸው:: ትልልቅ የአለት ድንጋዮች ከዛፎቹ አናት ላይ በድፍረት ፈጠጥ ብለው ይታያሉ፤ ብዛት ያላቸው ሸንተረሮች ዳገቱን ቆራርጠውት ይታያል::

ስምንት ማይሎች ከተጓዝን በኋላ፣ በረድፍ ከበቀሉ ዛፎች ዳር፣ ካምፑ በአሻጋሪ መታየት ጀመረ:: የቦታው ስም መሸከ ይባላል፤ ስሙን ያገኘውም ጋራ ላይ ባለ በደንብ በመከላከያ ከተሠራ መንደር ነው:: በጣም የሚያስደስት ቦታ ነበር፤ ከፍ ባሉ ተራሮች የተከበበ የመዝናኛ ፓርክ ይመስላል:: ወራጅ ውሃ፣ ሜዳማ የሳር ቦታና ግዙፍ የዋርካ ዛፍ ዋና ከፍሎቹ ናቸው::

1ኛው ብርጌድ እዚህ ቦታ በ15 ነበር የደረሰው፤ 2ኛው ብርጌድ መስጊ ካረፈ በኋላ በሁለተኛው ቀን ደረሰ::

የሚቀጥለው ጉዞ ወደ አፃላ ነው፤ ያም የሽፍታው መቀመጫ አምባላጌን አልፎ ነበር:: የአምባው ባለቤት ቀበሮው ወልደየሱስ አለዚያም ወልደ ያቆብ የሚባል ሰው ነው:: በአጠቃላይ በዚህ መንገድ ለሚያልፉ ለዎች ሁሉ አደጋ ነው:: በጋራው ላይ እንደ ንብ ቀፎ በተሠሩት መንደሮች ውስጥ፣ አሊቃው መጥራትና ማዘዝ የሚችለው አንድ ሺ፣ ጠንካራ፣ ጦር የያዙ ሰዎችና አምስት



የአፃሎ ካምፕ
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ሙቶ ጠመንጃ ያጉች አለው፡፡ ይህ አልፈን የምንሄድብት ቦታ የዋጂራት ክፍል ዋና ከተማ ነው፡፡ አምባው፣ ግራናይትና ላይም ስቶን ከሚባሉ አለቶች የተፈጠረ አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ሆኖ፣ ካለዩ ላይ ደግሞ በብዙ ሙቶዎች ጫማዎች ከፍታ ያለው ሾጠጥ ያለ ኮረብታ አለበት፡፡ አምባው፣ በሁሉም ጎን ቀጥ ያለ የሙቶ ጫማዎች ከፍታ ባለው ግድግዳ ከተራራው ላይ ይነሳል፡፡ የአምባው መሠረት ደግሞ ስፋቱ ወደ ሁለት ሙቶ ያርድ ኪዩብ ይሆናል፡፡ ወደ አምባው መውጫ ግማሹ ላይ፣ ወጣ ባለ ቦታ የተዋጊዎች መኖርያ ተሠርቶበታል፡፡ በሜዳ መነፀር ላየ ሰው፣ ብዙ ጠቆር ያሉ ፊቶች እኛን ቁልቁል ሲመለከቱ ማየት ይቻላል፡፡ እንደኔ አባባል፣ አዛዡ ራሱ ወልደ የሱስ ቢሆን ከጥሩ ቦታ ሆኖ እኛን እያየ ነው፤ የሚባለው እንኳን፣ ሰውየው ሥፍራውን ለቆ ሌላ ቦታ ሄዷል፤ ይህም፣ ናፒየር፣ በቀጥታ በሱ አምባ ሥር ለማለፍ በወሰነበት ሸር ያለበት ሁኔታ ምክንያት ነው፡፡


ለመጀመሪያዎቹ ስድስት ማይሎች፣ መንገዱ በጫካዎች ጥላ ሰር ነው የሚወስደው፤ አልፎ አልፎም የሚያሰፈራ ረግረግ፣ ወራጅ ውሀዎችና በሸለቆው ውስጥ የሚታዩ የእርሻ መሬቶች ይታያሉ፡፡ በድንገት ግን ወደ ዳገትነት ተቀይሮ፣ ለሁለት ማይሎች የሚሆን ከዚህ ቀደም በተጠቀሰው አምባ ዳገቶች ላይ ይወስዳል፤ ያም፣ ከአምባው ስር የሚገኝ ኮረብታ ጫፍ ላይ ከመውጣታችን በፊት ነው፡፡ ይህ ቦታ፣ ከካምፓችን ከመሸከ 1500 ጫማዎች በላይ ነበር፡፡

ከዚህ ከፍታ ላይ ሆነን አዲሱ ካማፓችን አፃሎን ማየት እንችላለን፤ ካለንበት ቦታ 2500 ጫማዎች ዝቅ ብሎ የሚገኝ ኩብ የመሰለ ሜዳማ ቦታ ነው፡፡ በእንጨት የተከበበ አረንጓዴ ይመስላል፡፡ በማወዳደር፣ በመሀከላቸው የሚታይ ጉልህ ልዩነት ግልፅ ነበር፤ በለምለም አረንጓዴ ቦታና፣ ዙሪያውን በከበቡት ኮረብታዎች መሀል፣ ኮረብታዎቹ ላይ ቆመን ቁልቁል ስንመለከትም በአስገራሚ የተፈጥሮ ሁኔታ በጣም ተደንቀን ነበር፡፡

በፊት ለፊት፣ በተቃራኒ የሚገኘውን፣ ከአምባው ጋራ እኩል ከፍታ ያለውን ቦታ ሳንወጣ፣ በሸለቆው አልፎ መሄዱ የሚመስል ነገር አልነበረም፡፡

ስለዚህ የነገው ጉዞ ገፅታ የሚያሰደስትም አይመስልም፡፡ ካፒቴን ጀ ሲድኒ ሪፓርት እንዳደረገው፣ ከመሸከ ወደ አፃሎ በተደረገው ጉዞ፣ ከአቢሲኒያውያን የጓዝ መስመር በኩል አንድ ሙቶ ስልሳ የሚሆኑ የጋማ ከብቶች ሞተዋል፡፡

ከዚህ ሞት ከበዛበት ጉዞ በኋላ፣ የጓዝ መስመሩ እስከሚቀጥለው ጥዋት ድረስ አልደረሰም ነበር፡፡ አንድ ወይም ሁለት የሚሆኑ "የተለዩ" ሌሊቱን በኮረብታው ላይ አሳለፉት፡፡



አምባላጌ (የወልደየሱስ አምባ)
(ዋቢ. መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ወልዴ፣ የያቆብ ልጅ ቸቫሊር ደ ፉሪዮሶ[108]፣ ከባህር ወለል አሰር ሺ ጫማዎች ከፍታ፣ በአምባላጌ፣ ምቾት ያላቸው ማረፊያ ከፍሎች ያሉት ሰው፣ ከብዙ ግፊት በኋላ፣ የከሩሴዶቹን አለቃ ወርዶ ለመገናኘት ተሰማማ፡፡

እንደሚበር ሰው እየከነፈ ሳይሆን፣ ኮራ ብሎ፣ ጠቆር ባሉ ሶስት መቶ የሚሆኑ ጠመንጃ በያዙ ሰዎች ታጅቦ ነበር፡፡ እነሱም ወደ ጠቅላይ አዛዡ ቢሮ ሊሄዱ፣ በሀሳባቸው ከእንግሊዝ ወታደር ጋራ ራሳቸውን እኩል በማድረግ ነበር፡፡ እህ፣ ያልተጠመቁ ተራ ሰዎች!

ወልዴ፣ በኩራት፣ ጌታ በመሰለ ሁኔታ ወደ ናፒየር ድንኳን ከገባ በኃላ፣ በሰፍራው በነበረው የካምፕ መቀመጫ ላይ ተኮፍሶ ተቀመጠ፡፡ ወንድሙ አብሮት ነበር፡፡ ወንድምየው ከአንድ ወላጅ የተወለደ አምሳያ ነው፤ ጎላ ያለ ቅንድብ፣ የተንጨባረረ ፀጉር፣ ቁንጥንጥና፣ ፈጠጥ ያሉ አይኖች ያሉት፣ ጎላ ያለ የጉንጭ አጥንቶች፣ ተለቅ ያሉ ጆሮዎች፣ ቀጠን ያለ ከንፈርና ሾጠጥ ያለ አገጭ ያሰው አጭበርባሪ ነው፡፡

ወልዴ ራሱ፣ አዋቂ ሰው ይመስላል፤ መካከለኛ ቁመት ሲኖረው፣ ደልደል ያለና ፈርጠም ያሉ ጡንቻዎች አለው፡፡ በምንም መንገድ ቢሆን መጥፎ መልክም አልነበረውም፡፡ ባህሪው ግን ይቅርታ የማይደረግለት ትዕቢት ነው ያሳየው፡፡ ልቆ መታየትና አጊጦ መታየትን መውደዱ፣ በእጆቹ ላያ ያደረጋቸው የወርቅ አምባሮች፣ እንደ ምሰሶ በቆመው አንገቱ ላይ ያደረገው ከብር የተሰሩ ሃብሎች፣ በአንበሳ ጋማ የተሸፈነው ያጌጠው ጋሻ፣ እናም ሌሎች በሱ ዙሪያ በሚታዩ ነገሮች መረዳት ይቻላል፡፡ ጠመንጃ ያዦቹ የታጠቁት የ6ኛው ክፍለ ዘመን የፖርቱጋል ፉሲሎችና ባለጥንድ አፈሙዝ ጠመንጃዎች ናቸው፡፡

ረዥም ውይይት ቀጠለ፡፡ ወልዴ፣ የሱ ሰዎች ለእንግሊዝ ሠራዊት ቀሰብ እንዲሸጡ የሚፈቀድ ለመሆኑ ቃል ገባ፤ ጠቅላይ አዛዡም ጥንድ አፈሙዝ ያለው ጠመንጃ ከነጥይቱና መያዣው ጋር፣ ከዚህ በተጨማሪም፣ ከአዲሱ ማር ተሪዛ ዶላሮች ለሱ ሰላሳ፣ ለወንድሙ ደግሞ ሀያ ዶላር ተሰጠ፡፡ በመጨረሻ ሰለ ቴዎድሮሰ ሲጠየቅ፣ ወልዴ ሲመልሰ፣ ቴዎድሮስ የሚዋጋ አይመስለኝም አለ፡፡ ሰጦታውን ካገኘ በኋላ ግን ወንድምየው የተለየ ነገር መናገር ጀመረ፡፡

እሱም እንዲህ አለ፤ "ወንድሜ ወልዴ አሁን ከተናገረው በተለየ እኔ የምመከራችሁ፣ ቴድሮሰ ይዋጋል፣ ትንፋሹ በሰውነቱ ውስጥ እሰካለ ድረስ ይዋጋል፤ እንደ ቀበሮ ብልጥ ነው፣ እንደ ጫካ ድመት(ጉልጉል ነብር) ፈጣን አይን አለው፣ እንደ አንበሳ ደፋር ነው፡፡ በድፍን ሌሊት በላያችሁ ላይ

108 (በምዕራፍ ሰባት ማስታወሻዎች)

ይወርዳል፡፡ ከሱ ተጠንቀቁ፣ አይኖቹን ከድኖም አያውቅም፤ ህልምም አያይም፡፡"

ናፒየር፣ "ወንድምህ ወልዴ ግን አይዋጋም ነው ያለው፡፡"

ወልዴ፣ "ይህን ያልኩት ልፈትሻችሁ ነው፡፡ ለእንግዳ ልባችን ከመስጠታችን በፊት፣ ደንባችን ነው፡፡ ወንድሜ በትክክል ነው የተናገረው፡፡ ቴድሮስ ኀበዝ ነው፣ ይገጥማችኋል፤ አይሸሽም፡፡ በሌሊት፣ ጭጋግ ከመልቀቁ በፊት ወይም ሲነጋ ከሱ ተጠንቀቁ፡፡"

ናፒየር፤ "አመስግናለሁ፤ በሉ ከኔ ጋር እንሂድና፣ ዝሆኖቻችንና ያሉንን ትልልቅ መሳሪያዎች እዩ፡፡"

አብረው ሄዱ፣ ዝሆኖችም የዝሆን መሪዎችን ትዛዝ በመቀበል፣ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ያሳዩ ጀመር፤ እንደ መተኛት፣ መንበርከከ፣ ድምፅ ማስማትና ዝስግሶ ማጥቃት ጨምሮ ነበር፤ ይህ ደግሞ ሁለቱን አለቆች በጣም አስገርሟቸዋል፡፡ የወታደር ባንዱ ሙዚቃ አስማ፤ የ33ኛው ሬጅመንት ደግሞ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን አሳየ፡፡ ሁለት ፈረሶች እንዲመጡ ከተደረገ በኋላ፣ ስወንድማማቾቹ ለእያንዳንዳቸው ሥጦታ ተሠጡ፡፡ ከዚህ በኋላ፣ ወዳጅነታቸውን በማረጋገጥ ወደ እምባቸው ተመለሱ፡፡ እነሱም ቢሆን በራሳቸው ባንድ አየተመሩ ነበር፤ ከቀንድ የተሠራ ጥሩምባ አየነፉ፣ መለከትና ዋሽንት አየነፉ፣ ሰስት ከር ያለው (ክራር) እየተጫወቱ ነበር፡፡ ለለር ሮበርት የሰጡት ስጦታ ደግሞ፣ ሁለት ጥሩ ጦሮች፣ ሁለት ጋሻዎች፣ ማር በምንቸትና ህያ አራት በሬዎች ነበሩ፡፡

ከአፃሎ በፊት፣ 16 ማይሎች ርቀት የሚገኘው ሙካን በመጋቢት 16 በ፲ኛው ብርጌድ ተያዘ፡፡

አምባላጌ፣ ከባህር ወለል በላይ 10ሺ ጫማዎች ከፍታ ላይ ስለሆነ፣ እናም የአፃሎ ሸለቆ ደግሞ ከአምባላጌ ጫፍ 2500 ጫማዎች ዝቅ ብሎ የሚገኝ ከሆነ፣ በአፃሎ የሚገኘው ካምፕ፣ ከባህር ወለል በላይ 7500 ጫማዎች ከፍታ አለው ማለት ነው፡፡ ሸለቆው የሁለት ማይሎች ስፋት አለው፤ ቦታው ከደረስን በኋላ ከፍታውን ወደላይ ስንመለከት፣ በጎንና በጎኑ ዳገታቸው አስቸጋሪ በሆነው በደብረ ሙሳ ኮረብታዎች ታጥሯል፡፡ ከፍታው፣ ከአምባላጌ ይልቅ ቀጥ ያለ ነው፤ ስለዚህ ጦሩ ዳገቱን ለመውጣት ከመሞከሩ በፊት መንገዱ ጠመዝመዛ ሆኖ መሠራት ነበረበት፡፡

ጦሩ መንገድ ከጀመረ በሁለት ሰአታት ውስጥ፣ ቀዳሚው ክፍል በተራራው ዳር መታየት ጀመረ፤ ከጦሩ በታች ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሌላ ሜዳ ነበር፣ ነገር ግን በጣም ተለቅ ያለና ከአፃሎ ጎድጓዳ ቦታ ጠለቅ ያለ ነበር፡፡

ወደታች ስንወርድ፣ ግማሹ ላይ የፒላጎ መንደርን አለፍን፤ ከመንደሩ በላይ በቀጥታ፣ ከዚህ በፊት ካየሁት ሁሉ በላይ በጣም የሚያምር የተፈጥሮ ስራ ይታያል። ብዙ ማዕዘን ያለው ተራራ ሲሆን፣ በሁሉም ጎኑ ቀጥ ያለ የአንድ ሺ ጫማዎች ከፍታ አለው፤ የተራራው አናት ሰስት ስኩዌር ማይል ስፋት አለው። በአገሬው ሰዎች፣ አምባ ደባር ተብሎ ነው የሚጠራው። ከአምባላጌ ጋራ እኩል ከፍታ አለው። እንዲህ አይነት የማየደፈር ቦታ ለምን በቴዎድሮስ ተዘነጋ ለሚለው ጥያቄ መልሱ፣ መቅደላ የበለጠ የማይደፈር ቦታ ሰስሆነ ነው ብሎ መገመት ይቻላል።

ከደብረ ሙላ ደቡብ በኩልና ከአምባ ደባር ግራ በኩል የሚገኘው ሜዳማ ቦታ ከደረስን በኋላ፣ ትንሽ ወራጅ ውሀ አቋረጥንና ከፍና ዝቅ የሚል ሳር ያደገበት መሬት ላይ ተጓዝን። ቀስ ብስንም ገላጣውን ሜዳ ትተን ቁጥቋጦ ባለበት መንገድ መጓዝ ጀመርን። እየደጋገመም፣ ዕይታው ይቀያየር ነበር፤ ያም የተለያዩ በተፍፀሮ ያደጉ ዛፎች፣ አበቦችና፣ ሜዳማ ቦታዎች፣ ሸንተረሮችን በሚያካትት ሁኔታ ገላጣ ፀሀያማ ሥፍራን ጨምሮ ነው። በአስራ ስድስት ማይሎች ጉዞ፣ በተፈጥሮ ባደጉ ዕፀዋት የተሞሉ የሚያዝናኑ ሸንተረሮችና ፈፋዎችን ተራ በተራ አልፈን የሙካን ካምፕ ያለበት ገላጣ ቦታ ፀሀይ ግባት ሲሆን ደረስን።



የአቢሲኒያ መልክተኞች በእንግሊዞች ካምፕ
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

# የምዕራፍ ሰባት ማስታወሻዎች

**ቁጥር 89፤** ከጦሩ ጋር የዘለቁት ጋዜጠኞች፣ ሄንሪ ስታንሊ ከ"ኒውዮርክ ሔራልድ"፣ ቪሰካውንት ኢዬር ከ"ዴይሊ ቴሌግራፍ"፣ ሲ እወሰቲን ከ "ታይምስ"፣ ጂ.ኤ. ሄንቲ ከ"ስታንዳርድ"ና "ፓዮኒር"፣ ሉተናንተ ኤፍ.ኤ ሼፓርድ በሬቃደኝነት ከቦምቤይ የሀንድ "ዴይሊ ነውስ" ና "ታይምስ"፣ ሉተናንት ዋይትሳይድ ከ "ሞርኒነግ ፖስት"፣ ከነዚህ ውጭ የጂአግራፊ ማህበር አባላትና የፈረንሳይ የፓለቲካ ዲፓርትሜንት ተወካይ ይገኙበታል:: ከጋዜጠኞቹ በተጨማሪ፣ በብሪታንያ ሳይጠየቁ፣ በራሳቸው ፍላጎት፣ በየመንግሥታቸው ተወከለው የመጡ ድምራቸው 13 የሚሆን መኮንኖች ተዘርዝረዋል:: የመጡትም፣ ከጣሊያን፣ ከፕሩሲያ፣ ከፈረንሳይ፣ ከኔዘርላንድስ፣ ከአውስትሪያና ከስፔይን ነበር::

**ቁጥር 101፤** ይህንን ጉዳይ፣ ራሳም እራሱ፣ መቅደላ ዙሪያውን ያሉ ባላባቶችን በማባበል መልከተኞቹ እንዲወጡና እንዲገቡ የረዱት መሆኑን ይጠቅሳል:: ራሳም፣ በዚህ ጉዳይ ላይ፣ ዋግሹም ገብዜ በጣም እንደተባበሩት ያትታል:: ቴዎድሮስ ለራሳም የሚያሳዩትን ወዳጅነት ያዩ የቴዎድሮስ ሰዎች እንኳን ሜና እስፈጠሩበትም:: ቴዎድሮስ መቅደላ ሲደርሱ ግን፣ ራሳም በራሳቸው ሰዎች አፍንጫ ስር የሠራውን ተንኮል ደርሰውበት መቅደላ የነበሩ አዛዦቻቸውን ወርፈዋል:: መቅደላ እስረኞችን ሲጠብቅ የነበረውን ጦር እንዳለ አዲስ ከሳቸው ጋር በመጣ ጦር ተክተውታል:: ይህም የነበረውን የውስጥ መላላክ ለማስቆም ነበር:: ይህ ርምጃቸው ለተወሰነ ጊዜ በመቅደላ እስረኞችና በእንግሊዝ ጦር መሀከል የነበረውን ግንኙነት እቋርጦት ነበር:: የሚገርመው ነገር፣ ራሳም፣ እቢሲኒያውያን ቃላቸውን ከሰጡ አያጥፉም በማለት እርሱን ይረዱ የነበሩ ሰዎችን ያመሰግናል::

**ቁጥር 99፤** ቴዎድሮስ፣ ደብረታቦር ላይ ሰዎችን በሳት ያቃጠሉበት ምክንያት ገለፃ ያስፈልገዋል:: ነገሩ እንዲህ ነው፤ የዳውንት ገዥ የነበሩ እቶ አዲሶ የሚባሉ፣ ከራስ ጉግሳ (ከራስ አሊ እያት) ጀምሮ እሊቃ የነበሩ ሰው ነበሩ:: ሰውየው መቶ አመት ያልፋቸዋል ተብሎ ተመዝግቧል:: በምንም አይነት መንገድ ቢሆን ለቴዎድሮስ ታማኝ ነበሩ:: ቴዎድሮስ እንኳን፣ "አባቸው" በማለት በአከብሮት ነው የሚጠሯቸው:: ግብር እንደሌላው ከፍል እልተጣለባቸውም፤ ነገር ግን ለመቅደላ የሚቀርብ ቀለብ ያስገቡ ነበር:: ሽማግሌው፣ መቅደላን ለመውጋት የሚመጣ ሽፍታን በሙሉ ድራሹን ነበር የሚያጠፉት:: ሆኖም፣ እንድ ሽፍታ ከሰማኒያ ሰዎች ጋር ሆኖ፣ በሌሊት የእሊቃው መንደር ገብቶ፤ ቤታቸውን በእሳት እቃጥሎ የሚያመልጠውን ሁሉ ጨረሰ:: ሽማግሌው ቀድመው ስለወጡ እሳቸውም ተገደሉ፤ ከሳቸውም ጋር ከሰምንት እስከ እስር የሚሆኑ ቤተሰቦቻቸው በሳት ነደዱ:: የእባቱን መሞት ያየው ልጃቸው፣ ከእምስት መቶ ሰዎች ጋር ሆኖ፣ አባቱን ሳይቀብር፣ ከኋላቸው በመከተል፣ ሽፍቶቹ እርፈው ብርንዶ ከሚበሉበት ቦታ በሁለት በኩል እስከብቦ ይይዛል::

ሽፍቶች አሊቃ እጁን አልሰጥም በማለቱ አዛው ተገደለና፣ አስከሬኑም ወደ ዳውንት ተመልሶ፣ ሜዳ ላይ ተጣለ:: ከሱ ጋር የነበሩ ሽፍቶች እጃቸውን ቢሰጡም፣ ለፍርድ፣ ወደ ንጉሡ ወደ አፄ ቴዎድሮስ፣ ወደ ደብረታቦር ተላኩ:: የሽማግሌውን መገደል ሰሙት ቴዎድሮስ አልቅሰው አንድ ቀን ሙሉ ሰው ሳያዩ ዋሉ:: ሽፍቶቹን ግን፣ ራሳቸው ባመጡት መንገድና የዳውንቱን አዛውንት ጌታና ቤተሰቦቻቸውን በገደሉበት መንገድ፣ በጎጀ ተዘግተው በሳት እንዲቃጠሉ ተደረገ:: ይህ ዜና በምዕራባውያኑ በኩል ተጋኖ ሲነገር ይታያል:: በተቃራኒው ግን የደላንታው ገዥ፣ አርቅና፣ የራሳም ወዳጅ እንደነበርና ተላላኪዎችን ሁሉ አይደበቀ ይረዳው እንደነበር ተዘግቧል:: ራሳም፣ የደላንታውን ገዥ ከሁለት ወንድሞቹ ጋር፣ ታማኞች ይላቸዋል:: ራሳም፣ ስለ ዳውንት፣ ሰው በቤት እንዳለ መቃጠሉን ሲገልፅ፣ ሌቦቹ ያደረጉትን ነገር አንስቶ፣ "ቴዎድሮስ ሌላ ጭካኔ ተማሩ::" ይላል:: ቴዎድሮስ በአከብሮት አርሰዎ እያሉ ከሚጠሯቸው አራት ሰዎች፣ አቶ አዲሶ አንዱ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ፣ ጳጳሱ፣ አፄ ዮሐንስ ሶስተኛ እና ደጃችዝማች ብሩ ነበሩ:: ደጃዝማች ብሩ ጎሹ፣ የጎጃሙ ገዥ የደጃች ጎሹ ልጅ ናቸው፤ ቴዎድሮስ እንደባለሟል ከደጃች ጎሹ ቤት ኖረዋል:: ደጃች ጎሹ ለጦርነት ሲሰለፉ፣ ቴዎድሮስ፣ በዚያን ጊዜ፣ ካሳ፣ አባከዎ አባትና ልጅ ነን ብለው እንዳይዋጉ ለምነው ነበር:: ይህም ልመና ቀጥሎ፣ ከልጃቸው ከብሩ ጎሹ ጋር ሲሰለፉ፣ ደጃዝማች ካሳ ብሩ ጎሹን ተው ብለው ለምነው ነበር::

**ቁጥር 102**፣ መንገዱን ከኋላ ደርሰው ያዩት እንግሊዞች በጣም እንደተደነቁበት ተገልጧል:: ቴዎድሮስ ራሳቸው ሠርተው የሚያሠሩ መሪ ነበሩ:: ከዚህ ቀደም እንደተጠቀሰው፣ ንጉሡ የመንገድን ጥቅም በጣም የተረዱት ይመስላል:: አንድ ጊዜ ከጋፋት ሲመለሱ፣ በመንገዱ ላይ የድንጋይ ቁልሎች ተከምረው ዘግተውት ነበር:: የድንጋዮቹ ብዛት፣ ከቴዎድሮስ ጋር አብረው ለነበሩት አውሮፓውያን እንኳን ተስፋ አስቆራጭ ነበር:: ሆኖም፣ ንጉሡ ከፈረሳቸው ወርደው ድንጋይ ተሸክመው ወደ ዳር መጣል ሲጀምሩ፣ ይህን ያዩ ተከታዮቻቸውና ሠራዊቱ ምሳሌውን በመከተል በአጭር ጊዜ ውስጥ መንገዱ እንዲከፈት አደርገዋል:: በሌላ አጋጣሚም እንዲሁ፣ ሀይለኛ ዝናብ ዘንቦ የአፈር ደለል መንገዱን ዘግቶ ፈረሰኛ ማሻገር ባልቻለበት ሰአት፣ ቴዎድሮስ ማንንም ሳያዙ፣ ራሳቸው በጦራቸው ደለሉን ሲቆፍሩ ያዩ አውሮፓውያን ዘግበውታል::

ይህን አይነት ሠርቶ የማሠራት ባህሪ፣ ካሳ ገና በሽፍትነት ጊዜ ነው የጀመሩት:: ቋራ ጠፈ ሆነ(ደረቅ) የሚታረሰም በጠፋ ጊዜ፣ ካሳ ራሳቸው ማካውን እየመነጠሩ፣ ወታደሮቻቸውም አብረው፣ ለእርሻ አዘጋጅተው አህልም ተዘርቶ አገሩ ተመልሶ ለም ሆኗል::

**ቁጥር 103**፣ ቀኛዝማች ገብረመድህን ልጅ ናቸው:: አባትዬው ቀኛዝማች ገብረመድህን ከራስ አሊ በኩል ሆነው ቴዎድሮስን ሲዋጉ ቆስለው ነበር:: ቴዎድሮስ ግን፣ አይዝዎት በማለት፣ መቶ ነፍጥ ሠጥተው በሹመት ወደግዛታቸው ወደ አገው መልሰው ልከዋቸው ነበር:: ሆኖም ቀኛዝማች ገብረመድህን፣ ምህረት

አድረገው መልሰው በሾሚቸው በአፄ ቴዎድሮስ ላይ ይሸፍታሉ፡፡ በግንቦት ወር፣ ገረገራ የሚባል ቦታ ላይ፣ ቴዎድሮስ የዋግሹሙን ጦር ወግተው መሪዎቻቸውን ማርከው፣ ቀሪዎችን ምህረት አድረገው ሲለቁ፣ በነበረው ህግ፣ በፍትህ ነገሥት አሰፈርደው፣ ዋግሹም ገብረመድህንን ከሌሎች ሰምንት ሰዎች ጋር በለቅላት ይቀጣሉ፡፡ ቦታው ረጅም ግራር ይባላል፡፡ ፀሐፊው ሲደመድም የከዱትን ገብረመድህን፣ እግዚአብሔር ከንጉሡ እጅ ጣላቸው ይላል፡፡ ቴዎድሮስ ወደ ዋግሹም ገብረመድህን ከመዝመታቸው በፊት ራሳቸው የገጠሙት ግጥም፣ "ጎጃምን ብንቀጣው በነፍጡ ተቀጣ፣ ወሎንም ብንቀጣው በእሳቱ ተቀጣ፣ ይብላኝ ለወራሄ ይብላኝ ለሰቆጣ፡፡" የሚል ነበር፡፡

ዋግ ሹሞች፣ የዋግ ግዛት ገዢዎች ነበሩ፡፡ ሥልጣኑ ከትልቁ ዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ወደ ሰለሞናዊው ሥርወ መንግሥት በመነኩሴው በአቡነ ተክለ ሀይማኖት አማካኝነት ሲዛወር የቀረውና የሚገዙት ግዛት ዋግ ብቻ ነበር ነበር፡፡ የየጁ ኦሮሞዎች፣ በጎንደር ቤተ መንግሥት ሆነው በጌምድር፣ ጎጃምን ሲገዙ፣ በራስ ጉግሣ ጊዜ፣ ዋግ በዋግሹም ከንፉ ሥር ነበር፤ ከንፉ ከራስ ጉግሣ በኩል የመጣውን ጥቃት ተከላከለው በሰላም ይኖሩ ነበር፡፡ በትግራይ፣ በዚያን ጊዜ ገዥው ራስ ወልደ ሥላሴ ነበሩ፡፡ ዋግሹም ከንፉ ሲሞቱ፣ ልጃቸው ዋግ ሹም ወሰን ተተኩ፡፡ አባታቸው ሲሞቱ፣ ትክክለኛው ወራሽ ዋግ ሹም ተፈሪ ሆነው እያለ፣ ቴዎድሮስ፣ ሥልጣኑን ለዋግ ሹም ገብረ መድህን ሠጡ፡፡ ገብረ መድህን ራሳቸው በናታቸው በኩል የዋግሹም ከንፉ የልጅ ልጅ ናቸው፡፡ ሆኖም ከላይ እንደተጠቀሰው ሲሸፍቱ፣ በቴዎድሮስ ተቀጡ፤ የተወነጀሉት በመክዳት ነበር፡፡ ቴዎድሮስ ዋግ ሹም ተፈሪን በቅርብ በማድረግ ከ10ሺ ሰዎቻቸው ጋር ወደ ራሳቸው ካምፕ ነው የወሰዷቸው፡፡ ዋግ ሹም ገብረ መድህን የላስታውን ገዥ የደጃች መሸሻን እህት አግብተው፣ ጎበዜና ብሩ የሚባሉ ሁለት ወንዶች ይወልዳሉ፡፡ ልጆቹ፣ የአባታቸውን መገደል ሲያዩ እንበቀላለን በማለት ሸፍተው ከርመው ነበር፡፡ ከሁለቱ፣ ጎበዜ ነበሩ ብዙ ጭፍራ የነበራቸው፡፡ የጭፍራቸውን ቁጥር የጨመረላቸው ነገር ደግሞ፣ እናታቸው፣ ከባለቤታቸው ሞት በኋላ፣ የዋድላውን ገዥ ደጃዝማች ወልደ ቂርቆስን አግብተው ለለነበር፣ ለወጣቱ ጎበዜ ተጨማሪ ሀይል እንዲያገኝ አድርጎታል፡፡ በውሰጥ እንደሚነበበው፣ አጎትየው ደጃች መሸሻ የዋግ ሹም ጎበዜ ጦር መሪና ተወካይ ነበሩ፡፡

**ቁጥር 104**፣ ደጃች ካሳ ምርጫ፣ መጀመሪያ በዋግሹም ጎበዜ የእንደርታ ገዥ ሆነው ተሹመው ነበር፡፡ ደጃዝማች ካሳ፣ የተምቤኑ ገዥ የደጃች ምርጫ ልጅ ናቸው፡፡ እናታቸው የእንደርታው፣ የደጃዝማች ድምፁ ልጅ ነበሩ፡፡ ደጃዝማች ድምፁ ራሳቸው የራስ ወልደ ሰላሴ የእህት ልጅ ናቸው፡፡ ሰለዚህ ካሳ ምርጫ በናትም ሆነ ባባታቸው ለሥልጣኑ ትክክለኛ ሰው ነበሩ፡፡ ዋግ ሹም ጎበዜ በእንደርታ ላይ እስኪሾሟቸው ድረስ ብዙም የሚታወቅ እንቅስቃሴ አልነበራቸውም፡፡ ከእንደርታው ሹመት በኋላ፣ በመጠናከር ጎበዜ ላይ ሸፍተው፣ ዋግሹም ጎበዜ ከሳቸው ጋር የሾሟቸውን የአጋሜውን ደጃች ደረሶን፣ ሀራማት በተባለ ቦታ ላይ ከፍተኛ ውጊያ በማድረግ

ርጃዝማቹን ካሸነፉ በኋላ ራሳቸውን ቻሉ:: ለትንሽ ጊዜ፣ የቴዎድሮስ ደጋፊ ሆነው ዩ፤ ያም ቴዎድሮስ የዋናው ጠላታቸው የጎበዜ ጠላት ስለነበሩ ነው:: ወዲያውኑ ን፣ በእኤአ 1867 አድዋ በመገስገስ የቴዎድሮስን ሹም ደጃች ባሪያን አሸንፈው ትግራይን ጠቅልለው ያዙ:: ጎበዜ፣ በላስታ ተቀምጠው ወደ ትግራይ ተሻግረው (እንግሊዞቹ በሚመጡበት መንገድ) ካሳን ለመውጋት አስበው ነበር:: በኋላ ግን የአፄ ቴዎድሮስን እንቅስቃሴ በመከታተል ብቻ ተወሰኑ::

ዋግሹም ጎበዜ ለእንግሊዞቹ ከፍተኛ ትብብር ቢያደርጉም፣ መሠረታዊ ምምነቱ፣ እንግሊዞቹ አሰፈሪውን ቴዎድሮስ ካሸነፉ በኋላ፣ ከአቢሲኒያ እንዲሰወሩ ነበር:: መልሰም፣ የመጀመሪያው የናፒየር አዋጅ ትልቅ ሚና እንደነበረው አይካድም::

እንግሊዞችን ያስቸገረ ብቸኛ መሪ ቢኖር ወልደየሱስ ነበር:: ወልደየሱስ፣ ካሳ ምርጫን አያምንም፤ ምንም እንኳን ለእንግሊዞች ቃል ቢገባ፣ ካሳ ይወጋኛል ብሎ ፈራል:: ወልደየሱስ፣ የራሱን ሰዎች ለእንግሊዞቹ ቀለብና ሌላም ነገር እንዳይሸጡ ከመከልከል በተጨማሪ፣ ሌሎች እንግሊዞችን የሚረዱ አቢሲኒያውያን በግዛቱ እንዳያልፉ ከልክሎ ነበር:: የእንግሊዞችን የቴሌግራፍ መስመር ለማጥቃት ሞክሮ ነበር፤ ነገር ግን ይህን ሃሳቡን የካሳ ጦር አከሸፎበታል:: የሚገርመው ነገር፣ እንግሊዞቹም ሆነ፣ አሜሪካዊው ፀሀፊ፣ ወልደየሱስን በከፋ ቀለም ሲቀቡትና ሲያወግዙት ነው የሚታየው:: እንደ ከለመንት መርካም አገላለጥ፣ ወልደየሱስን፣ የወዳጅ ወራሪዎችን ያስቸገረ ብቸኛው አቢሲኒያዊ መሪ ይለዋል:: ወንድምዬው ባሪያ ጊዮርጊስ ይባል ነበር:: ወልዴ፣ የቀዳሚው ጦር አዛዥ ኮሎኔል ፋይሬ(መርካም፣ ፊታውራሪ ፋይሬ ይለዋል) የመንገድ አቅጣጫ ሲጠይቀው፣ ቀጥተኛው በእርሱ አምባ ስር የሚያልፈው መንገድ እያለ፣ በማሳሳት ወደ ሌላ መርቶታል:: በዚህም ምክንያት፣ እንግሊዞቹ እስኪነቁ ድረስ የጦሩ ክፍል በከባድ መንገድ ሲንገላታ ከርሞ ጉዳዩ ከታወቀ በኋላ ግን ዋናው ጦር በቀጥተኛው መንገድ በአምባላጌ ስር ተጓዟል::

ቁጥር 108፣ ፀሀፊው ምን ለማለት ፈልጎ እንደሆነ ግልፅ አይደለም:: እንደ አፃፃፉ የወልዴና የወንድሙ ኩራትና ከእንግሊዞቹ ጋር የሚፈለገውን ያህል ስምምነት አለመፍጠራቸው ያናደደው ይመስላል:: ለዚህም ነው ስድብ የጨመረበት:: በዚህ ሁፍ እንደታየው፣ ከእንግሊዞች ጋር ያልተባበረ ሁሉ በከፋ አይን ብቻ ሳይሆን በከፋ ዞብ ነው የተቀመጠው:: ቴዎድሮስን ለአውሮፓ አንባቢዎች አከፊተው ቢፅፉ የሚገርም አይሆንም::